በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የገቢ ሂሳብ፣

1. ዩኒቨርሲቲው ለእያንዳንዱ ኮርስ በክሬዲት ሰዓት የተተመነ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ በቦርድ ጸድቆ በሠነድ መልክ ሳይኖር ከማታ፣ ከሳምንት መጨረሻ፣ ከክረምት እና ከርቀት ተማሪዎች ገቢ የሚሰበስብ መሆኑን ተረጋግጧል።
2. ዩኒቨርሲቲው በናሙና ከታየው የውስጥ ገቢ ከተለያዩ ድርጅቶች በቅጣት መልክ በድምሩ ብር 534,919.98 የሰበሰበው የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
3. በዩኒቨርሲቲው የሚሰበሰብ ገቢ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በባንክ በኩል የገባ ተብሎ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት በድምሩ ብር 11,296,938.37 የገቢው ዓይነት፣ ገቢው ከማን እንደተገኘ፣ የገቢው ምክንያት እንዲሁም የማስከፈያ ተመን/ታሪፍ ባለመታወቁ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ተረጋግጧል።

የወጪ ሂሳብ፣

4. የዩኒቨርስቲው ሠራተኞች በሥራ ገበታቸው እያሉና በሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ፈርመው እያሉ መስክ እንደሄዱ ተቆጥሮ ያለአግባብ በድምሩ ብር 13,884.00 ውሎ አበል መክፈሉን ተረጋግጧል፡፡
5. ዩኒቨርሲቲው ሥራ ለለቀቁ ሠራተኞች ብር 1,137.87 ብቻ ደመወዝ መክፈል ሲገባ፣ ብር 2,008.00 በመክፈሉ ብር 870.13 ያለአግባብ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፣
6. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 808,550.35 ለመስተንግዶ የተከፈለው የወጪውን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተጠቃሚ ብዛት፣ የተጠቃሚዎች ስም ዝርዝር፣ ተጠቃሚዎቹ ከየት እንደመጡ እና ለመጠቀማቸው በፊርማ ያረጋገጡበት የሚያሳይ ማስረጃ ከወጪ ሰነዱ ጋር ባለመያያዙ የወጪውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑንና የመስተንግዶው ግዥ ያለምንም ውድድር ከሁለት ድርጅቶች በቀጥታ ግዥው ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
7. ዩኒቨርስቲው በውሉ መሠረት ዕቃውን ላዘገዩ ድርጅቶቹ ባለመቅጣቱ ገቢ መሆን የነበረበት የቅጣት ሂሳብ በድምሩ ብር 7,406.09 ገቢ ሳይሆን መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡
8. ዩኒቨርስቲው የመደበኛ ስራ ያልሆነ በድምሩ ብር 6,026,898.10 ለተከታታይና ርቀት ትምህርት ፕሮግራም ክፍያው ከተከታታይ ትምህርት ገቢ ሂሳብ መፈጸም ሲገባው፣ ያለአግባብ ከመደበኛ በጀት ክፍያ ተፈጽሞ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
9. ዩኒቨርስቲው በሚመለከተዉ አካል ሳይፈቀድ በራሱ ተመን አውጥቶ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን Student clinic clinical activity payment እና Top Up Alowance ጥቅማ ጥቅሞችን ያለአግባብ በድምሩ ብር **451,072.00** ከህግ፣ ደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
10. ዩኒቨርስቲው በድምሩ ብር 419,754.99 ልዩ ልዩ አገልግሎት ለሰጡ ለግቢ የውበት ስራ፣ ወንበር ለጠገኑ፣ ሞጁል ላዘጋጁ በሚል ከህግ፣ ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ከመደበኛ በጀት ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
11. ዩኒቨርስቲው በተለያየ ጊዜ ያለምንም ውድድር በድምሩ የብር 1,507,994.06 የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ በቀጥታ ከየጆካ ሆቴል፣ ፍቃዱ አሶሬ (ከፋ ሆቴል) እና ኢንተርኮንትኔንታል አዲስ ሆቴል ቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
12. ዩኒቨርሲቲው ብር 429,986.96 የእሽግ ውሃ ግዥ ያለጨረታ (ያለምንም ዉድድር) በቀጥታ ከኤደን ቢዝነስ ኢ.ማ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

13.ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ የስራ ኃላፊዎችና ለአስተዳደር ሠራተኞች ከተፈቀደላቸው ጥቅማ ጥቅሞች ውጭ የርቀትና ተከታታይ ትምህርትን ላስተባበሩት በሚል በየደረጃቸው በተለያየ የክፍያ ተመን ከመደበኛ ሂሳብ በድምሩ ብር 694,717.78 ያለአግባብ ሳይፈቀድ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

14.ዩኒቨርሲቲው ከውስጥ ገቢ ለመደበኛ ተማሪዎች ቀለብ እንዲጠቀም በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ በድምሩ ብር **712,781.52** ያለአግባብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን እና ወጪውም ከውስጥ ገቢ በጀት ወጪ ሆኖ እያለ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ከመደበኛ በጀት ወጪ እንደተደረገ ተቆጥሮ ያለአግባብ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡፡

15.ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 1,034,508.00 ሂሳብ መደቡን ባልጠበቀ ሁኔታ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ወጪው በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ቢሆን በሂሳብ መደብ 6231 ብር 4,248,549.56 እና በሂሳብ መደብ 6251 ብር 3,654,283.18 ከበጀት በላይ የተጠቀሙ መሆኑን የሚያመለክት ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

16.ዩኒቨርሲቲው ብር 2,584,660.44 ባለ 5 ፎቅ የመምህራን መኖሪያ ቤት እና የእንግዳ ማረፊያ ህንጻ ዲዛይን የአገልግሎት ግዥ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን የህንጻና ከተማ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ዘርፍ ያለጨረታ (ያለዉድድር) በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

17.ዩኒቨርሲቲው ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ የሚሰበሰብ ወይም የሚወራረድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ዩኒቨርስቲው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ በድምሩ ብር **3,958,759.50** ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡
- በሂሳብ መደብ 4251 ለስራ ተቋራጮች የተያዘ የተሰብሳቢ ሂሳብ ለያንዳንዱ ስራ ተቋራጮች የተከፈተ ተቀጽላ ቋት የሌለው በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፡፡

<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

18.በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ከሚታይ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በድምሩ ብር **2,428,472.51** ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

በጀት፣

19. ዩኒቨርሲቲው ለመደበኛ በጀት ፕሮግራሞች ብር 15,773,733.19፣ ከውስጥ ገቢ ብር 1,663.56 እና ለካፒታል በጀት ፕሮግራሞች ብር 980,183.78 በድምሩ ብር 16,755,580.53 ለየሂሳብ መደቦቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የተጠቀሙ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
20. ዩኒቨርሲቲው ብር 4,349,001.00 ከሳህሌ ኃ/የተ/የግ/ማ የፈርኒቸር ግዥ ተፈጽሞ ክፍያ ሲፈጸም ዋናው (ኦርጅናል) የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ተቀብሎ ከሰነዱ ጋር ማያያዝ ሲገባው፣ በኮፒ ደረሰኝ የተያያዘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
21. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 8,664,065.70 ድርጅቶቹ የግንባታ ሥራ የተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ (Retention) በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ(PV) በዴቢትና በክሬዲት ለማሳየት ብቻ የተያዘ እና በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) በወጪ ሂሳብም ሆነ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት እና የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት በዚሁ የገንዘብ መጠን በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 21 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት ዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው ከተከታታይ ትምህርት ለትምህርት ክፍያ ተማሪዎቹ ባንክ አስገብተው ባንክ አድቫይስ ሲያመጡ ሂሳቡ የሚመዘገብ ቢሆንም፣ ብር 33,894.50 ተመዝግቦ ባንክ ገቢ የተደረገው የባንክ አድቫይስ ድምር 34,228.50 በመሆኑ በልዩነቱ ብር 167.00 ያልተመዘገበ ገቢ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በ2009 በጀት ዓመት ከተከታታይና ርቀት ትምህርት ፕሮግራም ሊገኝ የሚችለው የገንዘብ መጠን በዝርዝር የሚገልጽ የገቢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን እና የገቢ እቅድ ከክንውን ጋር በማነጻጸር ለመገምገም እንዲሁም የተሰበሰበው ገንዘብ መሰብሰብ በሚገባው መጠን የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፡፡

- በዩኒቨርሲቲው የተዘጋጀው ሂሳብ ሪፖርት የመደበኛ እና የውስጥ ገቢ በጥቅሉ የሂሳብ ሚዛኑን የሚያሳይ ቢሆንም፣ አንድ ላይ በመዘጋጀቱ ሁለቱንም ለይቶ ኦዲት ለማድረግ በየፋይናንስ ምንጫቸው ኦዲት ለማድረግ ሲሞከር፣
    - የውስጥ ገቢ የሳጥን ቋት (ሌጀር) ክሬዲቱ በብር 1,013,853.78 ዴቢቱን በልጦ የሚታይ ሲሆን፣ የመደበኛ የሳጥን ቋት ደግሞ በዚሁ የገንዘብ መጠን ዴቢቱ ክሬዲትን በልጦ የሚታይ መሆኑን፣
    - የውስጥ ገቢ የባንክ ቋት (ሌጀር) ዴቢቱ በብር 13,786,885.12 ክሬዲቱን በልጦ የሚታይ ሲሆን፣ የመደበኛው የባንክ ቋት ደግሞ በዚሁ የገንዘብ መጠን ክሬዲቱ ዴቢቱን በልጦ የሚታይ መሆኑና የመደበኛ እና የውስጥ ገቢ ሂሳብ በትክክል ተለይቶ በፋይናንስ ምንጩ ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣
    - የውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 10000149251368 በየወሩ መጨረሻ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ /Bank Reconciliation/ የማይዘጋጅ በመሆኑ የባንክ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም።
    - የዉስጥ ገቢ ሂሳብ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ተደርጎ የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ የማይሰራ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል።
- ለዩኒቨርስቲው የተመደበለት በጀትና ሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን፣ የመደበኛው በጀት ብር 4,700,071.38 እና የካፒታል በጀት ብር 139,379,026.28 በድምሩ ብር 144,079,079.66 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን ተረጋግጧል።
- ዩኒቨርስቲው እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በትምህርት ላይ ያሉ 163 መምህራን ለትምህርት የሄዱበት ጊዜ የማይታወቅ መሆኑን፣ 166 መምህራን ለትምህርት የሄዱበት ተቋም (የት እንደሚማሩ) የማይተወቅ መሆኑን፣ 174 መምህራን ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደሥራ የሚመለሱበት ጊዜ የማይታወቅ (በውሉ አልተቀመጠም) መሆኑ ተረጋግጧል።

<u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>

- የዩኒቨርስቲው የንብረት አስተዳደር ሲታይ በንብረት ደንብና መመሪያ መሠረት ዕቃዎች በአግባቡ ያልተያዙና ያልተወገዱ እንዲሁም የተዘረጋ የንብረት ቁጥጥር ስዓርት ባለመኖሩ ለረዥም ጊዜ በመቀመጣቸው ለብክነት እየተዳረገ መሆኑን፣

- የዩኒቨርስቲው የውስጥ ኦዲት አሰራርን እና አደረጃጀት በተመለከተ፡-
  - የ2009 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 30 ወጪ ሆኖ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ሲገባ ጥር 29/2009 መላኩ፣ የሁለተኛው ሩብ ዓመት እስከ ጥር 30 ወጪ ሆኖ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ሲገባ መጋቢት 29/2009 መላኩ፣የሶስተኛው ሩብ አመት እስከ ሚያዚያ 30 ወጪ ሆኖ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ሲገባ ግንቦት 14/2009 መላኩ፣የአራተኛ ሩብ ዓመት እስከ ነሀሴ 15 መላክ ሲገባ ህዳር 14/03/2010 የተላከ መሆኑን፡፡
  - የተሟላ የስራ ወረቀት/working paper/ ማለትም ስለተከናወነው ስራ በወጪ፣ በገቢ፣ በተሰብሳቢ፣ ተከፋይ ሂሳቦች ወዘተ የሚያሳይ መርሀ ግብር /audit programe/፣ የናሙና መጠን እና አመራረጥ የሚያሳይ የስራ ወረቀቶች የሌሉ መሆኑ፣
  - የውስጥ ኦዲት ክፍል በበቂ የሰው ኃይል ያልተደራጀ መሆኑ፡፡
  - ጥር 29/2009 በውስጥ ኦዲት ተዘጋጅቶ ለቀረበው የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት ገጽ 5 ላይ የውስጥ ኦዲት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠዉ ሥልጣንና ኃላፊነት መሰረት ይላል አዋጁ ለኦዲት ስራ ተጠይቆ ባለማቅረቡ ለግኝቶቹ የተቀመጠው ክራይቴሪያ (አዋጅ) ትክክል መሆኑን ለመገምገም ያልተቻለ መሆኑን፡፡
- የውል ስምምነት ሲገቡ ውል የገቡበትን ቀን 05/12/2007 ዓ.ም ብለው ቢቀመጥም ውሉ የሚጠናቀቅበት ቀነገደብ ባለመቀመጡ ውል ተቀባይ በውሉ ቀነገደብ ውስጥ ግዴታውን መወጣቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በአጠቃላይ ድርጅቶቹ ከአቅም በላይ ችግር ሲያጋጥማቸው በውሉ መሰረት በ3 ቀን ውስጥ ለዩኒቨርስቲው ለበፅሑፍ የማያሳዉቃቸውና የውሉ ቀነገደብ ከላፈ በኃላ እስከ 276 ቀይቶ ያመለከቱት ድርጅቶች መኖራቸውን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ዩኒቨርሲቲዉ የሰራተኞች የስራ ሰዓት መቆጣጠሪያ በ2009 በጀት ዓመት የፋይናስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሰራተኞች እና ለሰዉ ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሰራተኞች ለኦዲት ስራ ተጠይቆ ባለማቅረቡ በ2009 በጀት ዓመት

ለሰራተኞቹ የተከፈለዉ ውሎ አበል እና ደመወዝ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፡፡

<u>በ2008 ኦዲት ግኝቶች ላይ ስላልተወሰደ የእርምት እርምጃ፤</u>

- በ2008 ዓ.ቆጠራ ሲካሄድ ጠፍተዋል ተብለው የተገለፁ ንብረቶች ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተር ብዛት 29፣ ላፕ ቶፕ ብዛት 6፣የምግብ ቤት ጠረጴዛ ብዛት 13፣ ሚድየም ሀይ ባክ ወንበር ብዛት 12፣ ቴሌዝዥን ብዛት 3፣7 ኮምፒውተሮች፣ የሰባቱ RAM፣የኮምፒውተር ስፒከሮች (ብዛት 6)፣mouse(ብዛት 6)፣እንዲሁም አንድ LCD Projector፣ሪሲቨር ከፋሲሊቲ ልማት አስ/ዳ/ዳይሬክተር በቁጥር ወ/ዩ/5235/41/07 በቀን 20/08/07 ለወልቅጤ ከተማ ፖሊስ የተገለፀ ቢሆንም አሁን ድረስ መፍትሄ ያላገኘ መሆኑ፡
- አጋፔ ካፍቴሪያ የቤት ኪራይ ከሚያዚያ 2007 እስከ ሰኔ 2007 ብር 46,732.62፣እንዲሁም ከጥቅምት 2008 እስከ ግንቦት 2008 ብር 124,620.32 በድምሩ 171,352.94 ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ፡፡
- ሽናት ሽቀጣ ሸቀጥ የተባለውም በ2007 እና 2008 ዓ.ም በድምሩ ብር 7,351.95 ለዩኒቨርሲቲው የቤት ኪራይ ገቢ ያላደረገ መሆኑ፡-
- በ2008 በጀት ዓመት ውስጥ ከካፍቴሪያ፣ከሽቀጣ ሸቀጥ፣ከውበት ሳሎን፣ከፅህፈትና ፎቶ ኮፒ አገልግሎት መሰብሰብ የነበረበት ብር 11,177.9 ተሰብስቦ ገቢ ያልተደረገ መሆኑን፡፡
- ብር 75,240.00 በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ በሚከበረው የአረንጋዴ ኢኮኖሚ ልማት እና የ2007 ዓ.ም. የተማሪዎች ምረቃ በዓል በድምቀት ለማክበር በማለት የበዓሉ ቆይታ ጊዜው ሳይገለጽና የተሳታፊዎች ስማቸው ተመሳሳይ በሆነበት ሁኔታ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን፡፡
- ብር 104,376.00 ዩኒቨርሲቲው በመደበኛ የጥበቃ ሥራ ላይ ተሠማርተው ለሚሰሩ ሰራተኞች ሥራው በትክክል በትርፍ ሰዓታቸው ለመስራታቸው የሚያሳይ የሰዓት መቆጣጠሪያ ፊርማ እና በቀን የሚከፈላቸው የገንዘብ መጠን በሌለበት እንዲሁም ለማን እና እንዴት እንደሚከፈል የሚያሳይ የተሟላ የሰነድ ማስረጃ ሳይኖር ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ዩኒቨርሲቲው ለመምህራን የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት ሰጥቷቸው እያለ በተጨማሪ ለ75 (ሰባ አምስት) መምህራን በየወሩ ሀምሌ 2007- ሰኔ 2008ዓ/ም ጠቅላላ ብር 615,600.00 የቤት አበል ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሣብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የሳጥንና የባንክ ሂሳብ**

1.1 **ግኝት፣ የመደበኛና የዉስጥ ገቢ እንዲሁም የሳጥንና የባንክ ሂሳብ አንድ ላይ መመዝገቡን፣**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዉስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 8 ንፁስ አንቀጽ 1 ለዉስጥ ገቢ ራሱን የቻለ የሂሳብ መዝገብ መቋቋምና እያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ሂሳብ መደብ ተለይቶ መመዝገብ እንዳለበት እንዲሁም በዓመቱ መጨረሻ ተዘግቶ ለውጭ ኦዲተር መመርመር እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት የውስጥ ገቢ ሂሳብ ለብቻ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረጉን ኦዲት ሲደረግ የዉስጥ ገቢ ሂሳብ በመደበኛ ሂሳብ ጋር ተመዝግቦ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑና የሚለዩትም በፋይናንስ ምንጭ(የዉስጥ ገቢ “1900”፣ የመደበኛ “1800”) መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የተዘጋጀዉ ሂሳብ ሪፖርት የመደበኛ እና የዉስጥ ገቢ አንድ ላይ በመዘጋጀቱ ሁለቱንም ለይቶ ኦዲት ለማድረግ ያስቸገረን ሲሆን በፋይናንስ ምንጭ ኦዲት ለማድረግ ሲሞከር የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፣

- የዉስጥ ገቢ የሳጥን ሌጀር ክሬዲት በብር 1,013,853.78 ዴብቲን በልጦ የሚታይ መሆኑን፣
- የመደበኛ የሳጥን ሌጀር ዴቢት በብር 1,013,853.78 ክሬዲትን በልጦ የሚታይ መሆኑን፣
- የዉስጥ ገቢ የባንክ ሌጀር ዴቢት በብር 13,786,885.12 ክሬዲትን በልጦ የሚታይ መሆኑን፣
- የመደበኛ የባንክ ሌጀር ክሬዲት በብር 13,786,885.12 ዴቢትን በልጦ የሚታይ መሆኑና የመደበኛ እና የዉስጥ ገቢ ሂሳብ በትክክል ተለይቶ ተመዝግቦ ሪፖርት ባለመደረጉ የመደበኛ የሳጥን ሌጀር(ክሬዲት) የዉስጥ ገቢን የሳጥን ሌጀርን(ዴቢት) በማጠፋፋት የሳጥን ሌጀሩን ሚዛን ዜሮ አርጎታል እንዲሁም የመደበኛ የባንክ ሌጀር(ክሬዲት) የዉስጥ ገቢ የባንክ ሌጀር (ዴቢት) በማጠፋፋት የባንክ ሌጀር ሚዛን ዜሮ አድርጎታል፡፡

- የዉስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 10000149251368 በየወሩ መጨረሻ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ /Bank Reconciliation/ የማይዘጋጅ በመሆኑ የባንክ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የዉስጥ ገቢ ሂሳብ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ተደርጎ የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ የማይሰራ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

1.2 <u>ስጋት</u>፣

- ውስጥ ገቢ ከመደበኛው ሂሳብ ጋር የሚመዘገብ ከሆነ የውስጥ ገቢ እና የመደበኛ ገቢ ሂሳብን ከፍና ዝቅ አድርጎ በመደበቅ በትክክል የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን ላያሳይ ይችላል፡፡
- የዉስጥ ገቢ እና የመደበኛ በሳጥን እና በባንክ ያለዉ ገንዘብ በመጨረሻ ዓመት በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- የባንክ ሌጀር እና የሳጥን ሌጀር ትክክለኝነት ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

- የታዩት ችግሮች የተከሰተበት ሁነታ ተጣርቶ ተገብው ማስተካከያ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- የዉስጥ ገቢ ሂሳብ እና የመደበኛ ሂሳብ ሳይቀላቀሉ በትክክል ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፡፡እንዲሁም በየጊዜዉ የዉስጥ ገቢ እና የመደበኛ ሳጥን ዉስጥ ያለዉ ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ተደርጎ ከሳጥን ሌጀር ጋር መመዛዘን ይኖርበታል፡፡
- የፋይናንስ ክፍሉ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ እንዲያዘጋጅና በተወሰነ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እያደረገ የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ እንዲያዘጋጅ ጥብቅ መመሪያ ሊደርሰው ይገባል፡፡

1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

- በወቅቱ የውስጥ ገቢ ሪፖርት የማስተላለፍ ሂደት በሰው ሀይል እጥረትና በሰራተኞ የግንዛቤ እጥረት ምክንያት የተፈጠረ ችግር ሲሆን ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የልምድ ልዉዉጥ አደርገ በቀሰምነዉ የልምድ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የውስጥ ገቢን በተገቢው ለማስተዳደር ይሄንን ስራ የሚከታተል ፎካል ባለሙያ ለይተን በመመደብ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ሂሳቡ ተለይቶ የመመዝገብ ስራ እየሰራን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

- የውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ ተለይቶ ያልተሰራዉ ከላይ እንደተገለጸዉ የመደበኛና የዉስጥ ገቢ ተደባልቆ ይሰራ ስለነበረ ሲሆን በተሰጠን አስተያየት መሰረት ከዚህ በሀኋላ አስተካክለን የምንሰረ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- የውስጥ ገቢ ወጪ ሂሳቦችን ለይተን ባለመያዛችን የተፈጠረ ችግር ሲሆን ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ ማንኛውም የውስጥ ገቢና ወጪ ሂሳቦችን ለይቶ በመመዝገብ አሰራሩ ይበልጥ ክትትል እየተደረገበት ነው፡፡

2. የገቢ ሂሳብ፣

2.1.1 ግኝት፣ የገቢ ተመን /ታሪፍ እና የገቢ ዕቅድ አለመኖር፣

በከፍተኛ ትምህርት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 650/2001 ከቦርድ ኃላፊነት አንዱ ከፕሬዚዳንቱ በሚቀርብ ምክር ላይ ተመሥርቶ ተቋሙ ለትምህርት የሚያስከፍላቸዉን የተለያዩ ክፍያዎች አይነትና መጠንን ይወስናል ይላል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 መሰረት ዩኒቨርሲቲዉ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ዕቅድ አቀራረብ ባለፉት የበጀት ዓመታት የተሰበሰበውን ገቢ እና የሚኖሩ ለውጦችን ታሳቢ ማድረጉን በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሊሰበሰብ የሚችለውን የተለያዩ የመንግስት ገቢዎችን ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት የሚገባውን እና እንዲጠቀምበት የተፈቀደለትን ያካተተ ዕቅድ ማዘጋጀት እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ሕጎች ኦዲት ለማድረግ ሲሞከር፣

- ለእያንዳንዱ ኮርስ በክሬዲት አዎር የተተመነ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ በቦርድ ጸድቆ በዶክመንት መልክ ሳይኖር(በቦርድ ተመን /ታሪፍ ሳይወጣለት) ዩኒቨርሲቲው ከማታ፣ከሳምንት መጨረሻ፣ከክረምት እና ከርቀት ተማሪዎች ገቢ የሚሰበስብ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በ2009 በጀት ዓመት ከተከታታይና ርቀት ትምህርት ፕሮግራም ሊገኝ የሚችለው የገንዘብ መጠን በዝርዝር የሚገልጽ የገቢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን እና የገቢ እቅድ ከክንውን ጋር በማነጻጸር ለመገምገም እንዲሁም የተሰበሰበው ገንዘብ መሰብሰብ በሚገባው መጠን የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፡፡

2.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- በሚመለከተዉ አካል የተተመነ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ አለመኖር የገቢ ሂሳብን በዝርዝር ኦዲት በማድረግ አስተያየት ለመስጠት አያስችልም፡፡
- አስቀድሞ የተዘጋጀ የገቢ ዕቅድ የገቢ መሰረተ ግምት ከሌለ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ፣ አፈጻጸሙን ለመገምገምና የአጋጠሙ ክፍተቶችን ለመለየትም ሆነ ለአጋጠሙ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ሊያዳግት ይችላል፡፡

2.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ከተከታታይና ርቀት ትምህርት ፕሮግራም የሚሰበሰብ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ በዝርዝር የሚገልጽና በሚመለከተው አካል የጸደቀ(በቦርድ) ሠነድ ተዘጋጅቶ በጥንቃቄ እንዲጠበቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለፉት የበጀት ዓመታት የተሰበሰበዉን ገቢ እና የሚኖሩ ለዉጦችን ታሳቢ በማድረግ በበጀት ዓመቱ ዉስጥ ከመማር ማስተማር ሊሰበሰብ የሚችለዉን የገቢ መሰረተ ግምት ወይም የገቢ ዕቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

2.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- መደበኛ ካልሆነ ት/ት የሚሰበስብ ገቢን አስመልቶ የሰአት ክፍያ የማስከፈያ ዋጋ ተመን በተመለከተ ዩኒቨርሲቲያችን የተቋቋመዉ ጊዜ አጭር ከመሆኑ አንፃር ከነበረን የግንዛቤና የልምድ ማነስ ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ክፍተት በመሆኑ የማስከፈያ ተመን በሴኔት አፀድቀን ስናስከፍል የቆየን ቢሆንም በተሰጠን የኦዲት አስተያየት መሰረት ከዚህ በኋላ በቦርድ አፀድቅን የምናስከፍል መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ከላይ እንደተገለፀው ዩኒቨርሲቲያችን ከተቋቋመበት አጭር ጊዜ አንፃር በልምድ ማነስ ምክንያት የተፈጠረ ችግር በመሆኑ በቀጣይ የአካባቢያችን ማህበረሰብ የትምህርት ፍላጎትና ነባራዊ ሁኔታ አጥንተን እንዲሁም የሌሎች ዩኒቨረስቲዎች ልምድ ቀስመን በተሰጠን ኦዲት አስተያየት መሰረት ዝርዝር እቅድ ማዘጋጀት የጀመርን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.2.1 <u>ግኝት፣ተማሪዎች ገንዘብ ባንክ አስገብቶ ባንክ አድቫይስ አቅርቦ በገቢ ያልተመዘገበ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 5 አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀጽ 3 በመንግሥት የባንክ ሂሳብ ገቢ

ለተደረገ ገንዘብ የባንክ ደረሰኝ መስጠት እንዳለበት፣አንቀጽ 24 የመንግሥት ገንዘብ ለመሰብሰብ በሕግ ግዴታ የተጣለበት የእያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ለመንግሥት ገንዘብ አሰባሰብ ስርዓት መኖሩንና የመንግሥት ገንዘብ በሚገባ መሰብሰቡን ማረጋገጥ አለበት በማለት ይገልፃል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ዩኒቨርሲቲው ከተከታታይ ትምህርት ለትምህርት ክፍያ ተማሪዎቹ ባንክ አስገብቶ ባንክ አድቫይስ ይዞ መጥቶ ሂሳቡ የሚመዘገብ ቢሆንም፣

- በቀን 30/12/2008 በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 29770 በሂሳብ መደብ 1443 ብር 33,894.50 የተመዘገበ ቢሆንም ባንክ ገቢ የተደረገው የባንክ አድቫይስ ድምር 34,228.50 በመሆኑ በልዩነቱ ብር 167.00 ያልተመዘገበ ገቢ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

2.2.2 <u>ስጋት፣</u>

ከትምህርት የሚሰበሰበው ገቢ በትክክል በገቢ ደረሰኙ ላይ እየተመዘገበ ሪፖርት መሆኑን ላያሳየን ከማስቻሉም ባሻገር ሰነዶች በአግባቡ እየተያዙ እንዳልሆነ ሊያመላክት ይችላል፡፡

2.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ገንዘቡ ባንክ መግባቱን የሚያረጋግጥ የባንክ አድቫይስ ከገቢ ደረሰኙ ጋር መያያዝ ይኖርበታል፡፡የባንክ ደረሰኞቹም በትክክል እንዲመዘገቡ ለወደፊቱ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የባንክ አድቫይስ ስህተት በተመለከተ ቀደም ሲል የገቢ ካርኒ እንቆር የነበረዉ በጥቅል ድምር ስለነበር በልዩነት የታየው ብር 167 የውስጥ ገቢ በድምር ስህተት የተፈጠረ ችግር መሆኑ ታውቆ በቀጣይ በጥንቃቄ የምንሰራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

2.3.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ያለ ገቢ ደረሰኝ የተሰበሰበ የቅጣት ገቢ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2010 ክፍል 5 አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀጽ 1 የመንግሥት ገንዘብን መቀበል የሚቻለው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ስም ለሚሰበሰብ ማናቸውም ገንዘብ ተከታታይ ቁጥር ያለው በሚኒስትሩ ወይም በሚኒስትሩ በተሰጠ ውክልና መሠረት የተዘጋጀ ሕጋዊ ደረሰኝ መሰጠት አለበት በማለት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ

ዩኒቨርሲቲው በናሙና ከታየው ውስጥ ከተለያዩ ድርጅቶች በቅጣት መልክ በድምሩ ብር 534,919.98 የሰበሰበው ገንዘብ የገቢ ደረሰኝ ያልተሰጠ (ያልተቆረጠለት) መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡**ዝርዝሩ በአባሪ 1 ቀርቧል፡፡**

2.3.2 <u>ስጋት፣</u>

ከየድርጅቶቹ በቅጣት መልክ የሚሰበሰበው የገቢ መጠን በትክክለኛው መንገድ መሰብሰቡን በሪፖርቱ ላይ ላያሳይ ከመቻሉም ባሻገር ለብለሹ አሰራር በቀላሉ በር በመክፈት የመንግሥት ገንዘብ ብክነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.3.3 **<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>**

ከአቅራቢ ድርጅቶች በቅጣት መልክ ለሚሰበሰበው ገቢ ተከታታይ ቁጥር ያለው በሚኒስትሩ ወይም በሚኒስትሩ በተሰጠ ውክልና መሠረት የተዘጋጀ ሕጋዊ ደረሰኝ መሰጠት አለበት፡፡ ሪፖርትም ሊደረግ የሚገባው ከገቢ ደረሰኞቹ ማስረጃነት በመነሳት መሆን እንዳለበት አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ከተለያዩ ድርጅት በቅጣት የተሰበሰበ ብር 534,919.98 በተመለከተ፡- ከዚህ በፊት የቅጣት ገንዘብ በወጪ ማስመስከሪያ /PV/ የሂሳብ እንቅስቃሴ /እንቴሪዉን/ ከማሳየት ውጪ የገቢ ደረሰኝ የማንቆርጥ መሆኑንና ከአሁን በኂላ በተሰጠን አስተያየት መሰረት ለእያንዳንዱ ከፋይ የገቢ ደረሰኝ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.4.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የገቢው ዓይነት፣ገቢው ከማን እንደተገኘ፣የገቢው ምክንያት እና የማስከፈያ ተመን/ታሪፍ የማይታወቅ ገቢ፣</u>

በዩኒቨርሲቲው የሚሰበሰብ ገቢ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በባንክ በኩል የገባ ተብሎ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት በድምሩ ብር 11,296,938.37 የገቢው ዓይነት፣ገቢው ከማን እንደተገኘ፣የገቢዉ ምክንያት እንዲሁም የማስከፈያ ተመን/ታሪፍ፣ባለመታወቁ የገቢውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡ የሂሳብ ዝርዝር እንደሚካተለዉ ቀርቧል፡፡

ቀን	የገቢ ደረሰኝ ቁጥር	የገቢ ሂሳብ መደብ	ገንዘብ መጠን
30/10/2009	28813	1443	9,308,505.00
30/10/2009	28814	1443	996,516.80
30/10/2009	28815	1443	991916.57
		ድምር	11,296,938.37

2.4.2 ስጋት፣

የገቢዉ ደረሰኝ ተፈላጊውን መረጃ አሟልቶ ካልያዘ ወይም አግባብነት ባላቸው ሰነዶች ካልተደገፈ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥም ሆነ የተሟላ አስተያየት ለመስጠት አያስችልም፡፡

2.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የገቢ ደረሰኝ ተፈላጊውን መረጃ አሟልቶ እንዲይዙ አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች አባሪ በማድረግ ከገቢ ደረሰኝ ቅጠል ጋር እንዲያያዙ መደረግ አለበት፡፡ ለወደፊቱም የእርምት እርምጃ በመውሰድ አስፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.4.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ባንክ ገቢ ሆኖ በዝርዝር የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት 11,296,938.37 በተመለከተ፡- አብዛኛው የተከታታይ ት/ት ተማሪዎች በያሉበት አካባቢ በሚገኘው ባንክ ገቢ አድርገው የባንክ ደረሰኝ አምጥተው የገቢ ደረሰኝ ባለማስቆረጣቸው ምክንያት የተፈጠረ ክፍተት በመሆኑ በቀጣይ ከርቀትና ከተከታታይ ት/ት ዳይሬክቶሬት ጋር በመናበብ ጥቅል ገቢ በጥቅል የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠ ቢሆንም ከ2010 በጀት ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ በቦታው በቂ የሰው ሀይል በመመደብ በዝርዝር ገቢ ባስገባው አካል ስም መቁረጥ የጀመርን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3. የወጪ ሂሳብ፣

3.1.1 ግኝት፣ በኮፒ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የተከፈለ ክፍያ፣

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር4/2003 ዓ.ም ክፍል 3 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 7 ለሂሳብ ማወራረጃ በማስጃነት መቅረብ ያለበት ኦርጅናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ይገልፃል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ለክፍያዎቹ የሚቀርቡት ደጋፍ ሰነዶች ኦርጅናል መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ዩኒቨርሲቲው ብር 4,349,001.00

ክፍያ በኮፒ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ተዉቋል፡፡ የሂሳብ ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

- በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 568332 በቀን 14/03/2009 ብር 4,349,001.00 ከሳህሌ ጋ/የተ/የግ/ማ የፈርኒቸር ግዥ ተፈጽሞ የተከፈለ ሲሆን ክፍያ ሲፈጸም ዩኒቨርሲቲዉ ኦርጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ተቀብሎ ከሰነዱ ጋር ማያያዝ ሲገባው ኮፒ ደረሰኝ የተያያዘ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.1.2 <u>ስጋት</u>፣

በኦርጅናል ደረሰኝ ሌላ ክፍያ ሊፈፀም ይችላል፡፡

3.1.3 <u>**የማሻሻያ ሀሳብ**</u>፣

- ዩኒቨርሲቲዉ ኦርጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ለኦዲት ስራ ማቅረብ ይኖርበተራል፡፡ድርጅቱ ኦርጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ማቅረብ ካልተቻለ የተከፈለዉ ገንዘብ ወደመንግስት ካዝና ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡
- ለወደፊቱም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ለሚከፍሎዉ ገንዘብ ኦርጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መቅረቡ ተረጋግጦ እንዲከፈል አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

ኦርጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ አለመያያዙ ስለተገለጸዉ ጉዳይ ግኝቱ ትክክል ሲሆን ኦርጅናል ሰነዱፈልገን ከሰነዱ ጋር የምናያያዝ መሆኑንን እንገልጻለን፡፡

3.2.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>በሥራ ገበታቸው እያሉ መስክ ሄደዋል ተብሎ የተከፈለ የውሎ አበል</u>፣

የቀን ውሎ አበል መመሪያ ሰኔ/2004 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀፅ 2 መደበኛ የስራ ቦታው ከተማ ክልል ውጭ በመዘዋወር ሥራውን ለሚያከናውን የመንግስት ሠራተኞች ውሎ አበል እንደሚከፈል ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው ለሠራተኞች በሥራ ገበታቸው ላይ እያሉና በሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ፈርመው እያሉ መስክ እንደሄዱ ተቆጥሮ ያለአግባብ በድምሩ ብር 13,884.00 የውሎ አበል መክፈሉን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 2 ቀርቧል፡፡

3.2.2 ስጋት፣

ከውሎ አበል ደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ መፈፀም የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ምክኒያት ሊሆን ይችላል፡፡

3.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከመመሪያና ደንብ ውጭ ያለአግባብ ለዉሎ አበል የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይፈጸም ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

3.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የውሎ አበል ክፍያ የተፈፀመላቸው ሰራተኞች መስክ የወጡበትና ቢሮ የተገኙበት ጊዜ በማስታወሻ መዝግበው ባለመያዛቸው በውሎ አበል ሰንጠረዥ የቀን አሞላል ላይ የጥንቃቄ ጉድለት የተፈጠረ ችግር መሆኑ ታውቆ የተገለፀው ብር ከሰራተኞች ደመወዝ ተቆርጦ በአጭር ጊዜ ውስጥ የምናስመልስ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3.3.1 ግኝት፣ ዩኒቨርሲቲውን ለለቀቀ ሠራተኛ የተከፈለ ደመወዝ፣

የፌደራል የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ዓ.ም አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 'ሀ' ለደመወዝ ዝግጅት የሚከተሉት መረጃዎች መሟላት አለባቸው በሚለው ውስጥ የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች የክፍሉ ሠራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ ይህንንም መረጃ ወር በገባ በ 20 ኛው ቀን የፋይናንስ ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ያሳውቃል፡፡ በግልባጩም የአስተዳደር ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ያሳውቃል በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መመርያ መሠረት የደመወዝ ክፍያ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ዩኒቨርሲቲው በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 987533 በቀን 28/04/2009 ብር 2,008 ወ/ሮ ልክነሽ ጣሴ የተህሳስ ወር ደመወዝ የተከፈለለት ሰራተኛዉ በገዛ ፍቃደቸዉ በቀን 17/04/2009 ስራ የለቀቁ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ሰራተኛው ስራ ላይ የነበሩበት የ17 ቀን ብር 1,137.87 ብቻ ደመወዝ መክፈል ሲገባ ብር 2,008.00 በመክፈሉ ብር 870.13 ያለአግባብ ሰራተኛዉ የስራ ገበታዉ ላይ ሳይገኝ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.3.2 ስጋት፣

ዩኒቨርሲቲው ከሥራ ለተሰናበቱ ሠራተኞች ደመወዝ የሚከፍል ከሆነ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ደመወዝ ከመከፈሉ በፊት ሠራተኛው በሥራ ገበታው ላይ መኖር አለመኖሩን እና ሥራ መልቀቅ አለመልቀቁን በማጣራት ለሠራባቸው ቀኖች ብቻ ክፍያ እንዲፈፀም እና ላልሰሩባቸው ቀናት የወሰዱት ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱም አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በሂ/ም/ማ/ቁ 987533 ያለ አግባብ እላፊ የተከፈለ ደመወዝ ብር 870.13 በተመለከተ ክሊራንሱ ወደ ፋይናስ ክፍል ዘግይቶ በመድረሱ ምክንያት የተፈጠረ ስህተት ስለሆነ በዋሱ አማካኝነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ እንዲሆን እናደረጋል፡፡

3.4.1 ግኝት፣ ተጠቃሚዎቹ ያልታወቀ መስተንግዶ፣

ለመስተንግዶ ወጪዎች የተሟሉ መስረጃዎች ከክፍያ ሰነድ ጋር መያያዛቸዉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 808,550.35 ለመስተንግዶ ወጪ ተደርጎ የተከፈለ ሲሆን የክፍያዉን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተጠቃሚ ብዛት፣የተጠቃሚዎች ስም ዝርዝር፣ማን ምን እንደተጠቀመ፣ተጠቃሚዎቹ ከየት እንደመጡ እና ተጠቃሚዎቹ ለመጠቀማቸዉ በፊርማ ያረጋገጡት የሚያሳይ መስረጃ ከወጪ ሰነዱ ጋር ባለመያያዙ የወጪዉ ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑና እንዲሁም የመስተንግዶ ግዥ ያለምንም ዉድድር ከሁለት ድርጅቶች በቀጥታ ግዥዉ ተፈጽሞ የተከፈለ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሂሳብ ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 570161 በቀን 13/08/2009 ብር 597,010.70 የመስተንግዶ ግዥ ከጃካ ሆቴል ለ55ኛዉ የዓለም የቴአትር ቀን ሲከበር ተብሎ ለአልጋ፤ለምግብ፣ለለስላሳ መጠጦች፣ለቢራ መጠጦች እና ለሻይ ቡና አገልግሎት ግዥ ተፈጽሞ የተከፈለ ቢሆንም የክፍያዉን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተጠቃሚ ብዛት፣የተጠቃሚዎች ስም ዝርዝር፣ማን ምን እንደተጠቀመ፣ተጠቃሚዎቹ ከየት እንደመጡ እና

ተጠቃሚዎቹ ለመጠቀማቸዉ በፊርማ ያረጋገጡት የሚያሳይ መስረጃ ከወጪ ሰነዱ ጋር ባለመያያዙ የወጪዉ ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን እንዲሁም የመስተንግዶ ግዥ ያለምንም ዉድድር ከጆካ ሆቴል በቀጥታ ግዥዉ ተፈጽሞ የተከፈለ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 569458 በቀን 12/10/2009 ብር 211,539.65 የመስተንግዶ ግዥ ከየብሳቢ ሆቴል ለ5ኛዉ ሀገር አቀፍ የተማርዎች ቀን የመስተንግዶ አገልግሎት ክፍያ ተብሎ ለአልጋ፤ለምግብ፣ለለስላሳ መጠጦች፣ለቢራ መጠጦች እና ለሻይ ቡና አገልግሎት ግዥ ተፈጽሞ የተከፈለ ቢሆንም የክፍያዉን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተጠቃሚ ብዛት፣ የተጠቃሚዎች ስም ዝርዝር፣ ማን ምን እንደተጠቀመ፣ተጠቃሚዎቹ ከየት እንደመጡ እና ተጠቃሚዎቹ ለመጠቀማቸዉ በፊርማ ያረጋገጡት የሚያሳይ መስረጃ ከወጪ ሰነዱ ጋር ባለመያያዙ የወጪዉ ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን እንዲሁም የመስተንግዶ ግዥ ያለምንም ዉድድር ከየብሳቢ ሆቴል በቀጥታ ግዥዉ ተፈጽሞ የተከፈለ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.4.2 ስጋት፣

- ክፍያዉ የተሟላ ደጋፊ ሰነድ ከሌለ የወጪዉን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ሊያስቸግር ይችላል፡፡
- የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ለብዝበዛ ሊዳረግ ይችላል፡፡
- ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ይህም ቁጠባን፣የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፣
- ማንኛዉም ግዥ የግዥ መመሪያ ተከትሎ አለመፈፀም ተጠያቂነት ከማስከተሉም በላይ ለመንግስት ገንዘብ ሚዝበራ መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

3.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ዩኒቨሲቲዉ ለክፍያዉ የተሟላ ደጋፊ ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ለወደፊቱም ማንኛዉም ክፍያዎች ከመፈጸሙ በፊት የክፍያዉን ትክክለኝነት የሚያረጋግጡ የተሟላ የክፍያ ምስክር(ደጋፊ ሰነድ) ከወጪ ሰነዶች ጋር መቅረቡን አረጋግጦ ክፍያ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው የመንግሥትን ገንዘብ ከብክነት እና ከምዝበራ ለመከላከል ማንኛውም ግዥ መፈፀም ያለበት መንግሥት ባወጣው የግዥ ስርዓት መሆን ይኖርበታል፡፡

3.4.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ከሁለት ሆቴል ብቻ ግዥው የተፈፀመበት ምክንያት ከተለያዩ ቦታ የሚመጡ ተጋባዥ እንግዶቻችን ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚችሉ በከተማው ውስጥ ያሉት ሁለቱ ሆቴሎች ብቻ በመሆናቸው፤ የመኪና ማቆሚያ፣ የኢንተርኔት፣ የዋይፋይ እና በአጠቃላይ የሆቴል አገልግሎት ጥራት ደረጃ የተሻለ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ተወያይቶበት ከሁለቱ ድርጅቶች ግዥው እንዲፈፀም በወሰነው ውሳኔ መሰረት የተፈፀመ ቢሆንም ከአሁን በኋላ ከላይ የተገለፀው መመዘኛዎች በማውጣት አወዳድረን ግዥ የምንፈጽም መሆኑን እየገለጽን እንዲሁም የስልጠና/ የስብሰባ ፕሮፖዛል የተሳታፊዎች አቴንዳንስ እና የመሳሰሉት ደጋፊ ሰነዶች ከወጪ ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረቡን እያረጋገጥን ክፍያ የምንፈፅም መሆኑን እንገልፃለን፡፡

3.5.1 ግኝት፣ ዕቃውን ላዘገዩ ድርጅቶች የቅጣት ሂሳብ አለመታሰቡ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 ፊደል ሸ እና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 27/4 ፊደል ሀ መሰረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን ፣የግንባታ ዘርፍ ሥራውን አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየው ጊዜ ሳይፈፅም በቀረዉ የውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛውን መቀጣት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው በውሉ መሠረት ዕቃውን ላዘገዩ ድርጅቶቹ ባለመቅጣቱ ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት የቅጣት ሂሳብ በድምሩ ብር 7,406.09 ገቢ ሳይሆን መቅረቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ እደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	ዩኒቨርሲቲው ያራዘመበት ቀን ገደብ	የተከፈለው	ድርጅቱ በውሉ መሰረት ንብረቱን ገቢ ማድረግ የነበረበት እስከ ቀን	ንብረቱ ገቢ የሆነበት ቀን	ድርጅቱ ንብረቱን ላዘገየበት በውል መሰረት መቀጣት የነበረበት	ተቀጥቶ የተገኘ	ልዩነት/ገንዘብ መጠን/
1	1/3/2009	568376	የፈርኒቸር ዕቃ ግዥ	የለም	ለደመቀ ንጉሴ የእንጨትና ብረታ ብረት የግል አነስተኛ ኢንተርፕ	03/13/2008	15/02/09	0.001*669,058.50=669.58*46ቀን=30,1776.66	27,344.13	**3,432.54**

					ራይዝ					
2	29/9/2009	0846456	የላብ ራቶሪ ዕቃ ግዥ	የለም	ልዑል ገ/ጊዮርጊስ የመሳሪያ፣መገ ልገያ እና አቅርቦቶች አስመጪ	28/08/2009	5/09/09	0.001*5,077,313.25 =5,077.31*6ቀን=30, 463.88	26,490.33	**3,973.55**
አጠቃላይ ድምር									53,834.46	7,406.09

3.5.2 ስጋት፣

ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት ገቢ እንዳይገባ ከማድረጉም በሻገር አፈጻጸሙ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ከአቅራቢዎች ጋር በሚገባዉ ውል መሰረት ንብረቱ ገቢ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነቱን ሊወጣ የሚገባ ሲሆን በገቡት ውል መሰረት ኃላፊነታቸውን በማይወጡ አቅራቢዎች ላይ በየቀኑ አቅራቢው ሳይፈፅም በቀረው የውል መጠን ላይ 1/1000ኛ ቅጣት ማስከፈል ያለበት ሲሆን ዩኒቨርሲቲዉ ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት ያልተሰበሰበዉ ቅጣት ገንዘብ ብር 7,406.09 ከየድርጅቶቹ ላይ ገቢ እንዲሆን ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸው ካልተወጡ አቅራቢዎች ያልተሰበሰበው ብር 7,406.09 በተመለከተ የቅጣቱ ገቢ ስናሰላ የነበረዉ ቫትን ሳያካትት በነበረው የዋጋ መጠን መሰረት የተሰላ በመሆኑ ምክንያት የተፈጠረ ስህተት ስለሆነ በቀጣይ በልዩነት የተመዘገበው የቅጣት ገንዘብ የምናስመልስ መሆኑ እናሳውቃለን፡፡

3.6.1 ግኝት፣ የመደበኛ ስራ ያልሆነ ከመደበኛ ስራ የተከፈለ፣

የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ እንደሆነ ያዛል፡፡ በዚሁ መመሪያ መሰረት ከመደበኛው በጀት የተፈፀሙ ክፍያዎች ዩኒቨርሲቲው በመደበኛው ስራ ለሚያከናውነው ተግባራት ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ከተየዉ ዉስጥ በድምሩ ብር **6,026,898.10**

ለተከታታይና ርቀት ት/ት ፕሮግራም የወጣው ወጪ ክፍያዉ ከተከታታይ ትምህርት ገቢ ሂሳብ ላይ መፈጸም ሲገባ ያለአግባብ ሳይፈቀድለት ከመደበኛ በጀት ክፍያ ተፈጽሞ በመደበኛ ፋይናንስ ምንጭ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅጥ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሂሳብ ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	ገንዘብ መጠን	የወጪዉ ምክንያት
1	28/08/09	282195	159,014.00	በዱራሜ ሆስፒታል የ3ኛ ዓመት የግል የጤና ተማሪዎችን ላስተማሩት እና ላስተባበሩት በሚል
2	28/08/09	282194	78,180.00	በተከታታይና ርቀት ት/ት ፕሮግራም በርቀት የሚወስዱ የት/ት ዓይነቶች ሞጁል ያዘጋጁ በሚል
3	28/03/09	987527	487,762.00	የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም የማታ ት/ት ከጫና በላይ ያስተማሩት በሚል
4	28/03/09	987527	110,520.00	በተከታታይና ርቀት ት/ት ፕሮግራም ለተማሪዎች ሞጁል ያዘጋጁ በሚል ክፍያዉ የተፈጸመ ሲሆን
5	28/07/09	987541	323,366.50	የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም በክሬምት ከጫና በላይ ያስተማሩት በሚል
6	28/06/09	987539	3,538,438.00	የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም የማታ ት/ት ከጫና በላይ ያስተማሩት በሚል
8	13/03/09	568898	60,488.60	በተከታታይ ርቀት ት/ት ፕሮግራም በክረምት ሴሚስተር ላስተማሩት በሚል
9	12/04/09	569029	59,890.00	በተከታታይ ርቀት ት/ት ፕሮግራም በክረምት መርሀ ግብር ለሚማሩ ተማሪዎች ሞጁል ያዘጋጁት በሚል
10	13/03/09	987548	964,653.00	በተከታታይ ርቀት ት/ት ፕሮግራም የማታ ፕሮግራም ላስተማሩት በሚል
11	28/10/09	173052	244,586.00	በተከታታይ ርቀት ት/ት ፕሮግራም የማታ ፕሮግራም ላስተማሩት በሚል
		ድምር	**6,026,898.10**	

3.6.2 ስጋት፣

- መንግስት ለመደበኛ ስራ የሚመድበዉ በጀት ያለአግባብ ላልታለመለት አላማ ሲዉል ይችላል፡፡
- ዩኒቨርሲቲዉ በመደበኛ ስራ ለመስራት አቅዶ የተመደበለት በጀት ለታቀደለት አላማ ከልዋለ እቅዱን ላያሳካ ይችላል፡፡

3.6. 3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ዩኒቨርሲቲው ያለአግባብ ከመደበኛ በጀት ሂሳብ እየተከፈለዉ ያለዉ የተከታታይና ርቀት ትምህርት ፕሮግራም ወጪዎች አግባብነት የሌለው በመሆኑ ከመደበኛ በጀት

የተከፈለው ወጪ ከተከታታይ ትምህርት ገቢ ሂሳብ ወደ መደበኛ ሂሳብ ክፍያው በማዞር የማስተካከያ እርምጃ ተወስዶ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

- ለወደፊቱም የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ወጪዎች መመሪያዉ በሚፈቅደዉ መሰረት ከተከታታይ ትምህርት ገቢ ሂሳብ ላይ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

3.6.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የውስጥ ገቢ እና የመደበኛ ሂሳብ ምዝገባ ለያይተን ባለመያዛችን ምክንያት የተፈጠረ ክፍተት ሲሆን ቀደም ሲል በነበረው የአሰራር ልምድ ከመደበኛ በጀት ላይ የተከታታይና የርቀት ትምህርት ይከፈል እንደነበር እንዲሁም ከተከታታይ ት/ት ገቢ ላይ ለመደበኛ በጀት ወጪ ክፍያ ይፈፀም የነበረ በመሆኑ ሆኖም ግን ከዚህ በጀት ዓመት ጀምሮ የውስጥ የመደበኛና የዉስጥ ገቢ በመለያየት የሚከታተል ባለሙያ መድበን እየሰራን እንገኛለን፡፡

3.7.1 ግኝት፣ ከድርጅቶች ላይ ተቀንሶ የሚያዝ መያዣ (Retention) በወጪም ሆነ በተከፋይም ተመዝግቦ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ክፍል 7 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 5 ፊደል ለ ለማናቸዉም የግንባታ ዘርፍ ስራ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሰረት ከሚፈፀመዉ ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራዉ ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% (አምስት በመቶ) በመያዣ መልክ ተቀንሶ ይያዛል ብሎ ይደነግጋል፣ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንፁስ አንቀጽ 5 ፊደል ሠ ላይ የተከፋይ ሂሳብ እንቅስቃሴዎች በእለቱ በሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሂሳብ ሌጀር ላይ መወራረስ አለበት ብሎ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ከግንባታ ስራዎች ላይ በመያዣነት(Retention) ከሚከፈለዉ ክፍያ ላይ በትክክል ተቀንሶ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረጉን ኦዲት ሲደረግ በናሙና ከታየዉ ዉስጥ በድምሩ ብር 8,664,065.70 ድርጅቶቹ የግንባታ ስራ ሰርተው ካቀረቡት ላይ የተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ(Retention) በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ(PV) ላይ በዴቢትና በክሬዲት ለማሳየት ብቻ የተያዘ ሲሆን በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ(TR) ላይ በወጪ ሂሳብም ሆነ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት ዉስጥ ያልተካተተ በመሆኑ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት እና የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት በዚሁ የንዘብ መጠን በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ **ዝርዝሩ በአባሪ 3 ቀርቧል፡፡**

3.7.2 ስጋት፣

ከመንግስት የሚፈለግ ገንዘብ በትክክል ላይታወቅ ይችላል፡፡

3.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ዩኒቨርሲቲዉ ድርጅቶቹ የግንባታ ስራ ሰርቶ ክፍያ ሲጠየቅ ድርጅቱ ለሰራዉ ስራ የሚከፈል ክፍያ በወጪ ሂሳብ መደብ በዴቢት መመዝገብ እንዲሁም ሰርቶ ከቀረበዉ ክፍያ ላይ የሚቀነስ የመያዣ ሂሳብ በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5061 በክሬዲት በትክክል በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሂሳብ ሌጀር ላይ መወራረስ አለበት፡፡ ዩኒቨርሲቲዉም በወጪ እና በተከፋይ ሲመዘግብ፣

6324----------------XXX

4251--------------------xxx
5006--------------------xxx
5059--------------------xxx
5061--------------------xxx
4103--------------------xxx

በመጨረሻዉ ርክክብ የመያዣ ክፍያዉ ጥያቄ ሲቀርብ፡፡

5061-----------xxx

4103--------------xxx

- ዩኒቨርሲቲዉ ከያንዳንዱ ስራ ተቋራጮች ላይ ቀንሶ ያስቀረዉን ሂሳብ በተከፈይ ሂሳብ መዝግቦ በመያዝ እንዲሁም ለያንዳንዱ ስራተቋራጮች ተቀጽለ ሌጀር በመክፈት መቆጣጠር ይኖርበታል፡፡

3.7.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ከህንጻ ተቋራጮች የሚቀነሰዉን የመያዣ ሂሳብ በተከፋይነት /በእዳነት በነብስ ወከፍ ሌጀር ያልተመዘገበ ቢሆንም ክፍያ በምንፈጽምበት ወቅት ኢንትሪዉን ስናሳይ የነበረ ሲሆን በቀጣይ ግን በተሰጠን አስተያየት መሰረት የነብስ ወከፍ ሌጀር በእያንዳንዱ ተቋራጭ ስም በማዘጋጀት የቁጥጥር ስራ የምንሰራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

3.8.1 ግኝት፣ በሚመለከተዉ አካል ሳይፈቀድ ያለአግባብ የተከፈለ ጥቅማጥቅም፣

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ 30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ በሥራ አመራር ቦርድ የሚመሩ አንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሰራተኞችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለሥራ አመራር ቦርድ እያቀረቡ

በማስወሰን ተግባራዊ ማድረጋቸዉን ገልጾ ይህ ጉዳይ የሚንስትሮች ምክርቤት በ4ኛዉ የምርጫ ዘመን 15ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ተነስቶ ዉይይት ከተደረገበት ቦኃላ "ከጠቅላይ ሚኒስተር ጽ/ቤት እዉቅናና ፈቃድ ዉጭ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ/በቦርድ/የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስካሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች ባስቸኳይ እንዲቋረጡ" መመሪያ አስተላልፏል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ከመደበኛ በጀት የሚከፈለዉ ጥቅማጥቅሞች ሲታይ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን Student clinic clinical activity payment እና Top Up Alowance በሚል ዩኒቨርሲቲዉ በራሱ ተመን ያወጣለት በድምሩ ብር 451,072.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፣ ክፍያውም በሚመለከተዉ አካል ሳያስፈቅድ ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሂሳብ ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ቀን	የወጪ ማስመስረሪያ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የተከፈለበት ወር	ለአንድ ሰራተኛ በወር የሚከፈል	ተከፈለ	የገንዘብ መጠን
28/08/2009	987546	Student clinic clinical activity payment	ሚያዝያ ወር	1,333.00	ለ18 ሰራተኞች	23,994.00
28/06/2009	987539	Student clinic clinical activity payment	የየካቲት ወር	1,714.00	ለ14 ሰራተኞች	23,996.00
28/09/2009	987548	Student clinic clinical activity payment	ግንቦት	1,333.00	ለ18 ሰራተኞች	23,994.00
28/10/2009	173052	Student clinic clinical activity payment	ሰኔ	1,333.00	ለ18 ሰራተኞች	23,994.00
29/09/2009	987548	Top Up Alowance	መጋቢት ሚያዝያ እና ግንቦት	3,850.00	ለ21 ሰራተኞች	242,550.00
28/10/2009	173052	Top Up Alowance	ሰኔ	3,850.00	ለ23 ሰራተኞች	88,550.00
28/07/2009	987541	Student clinic clinical activity payment	የመጋቢት	1,333.00ለ	ለ18 ሰራተኞች	23,994.00
ጠቅላላ ድምር						451,072.00

3.8.2 <u>ስጋት፣</u>

- በመመሪያ ያልተደገፈ ክፍያ መፈጸም ለመንግስት ገንዘብ ምዝበራ መንስኤ ከመሆኑም በላይ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ጥናት ተደርጎ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ያልጸደቀ ጥቅማጥቅም የክፍያዉ ትክክለኝነት ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡
- የመንግሥትን መመሪያ የጣሰ ክፍያ ከመሆኑም በተጨማሪ አንድ ሠራተኛ ለሚከፈለው ደመወዝ ለሚሰራው ሥራ ያለአግባብ ተጨማሪ ክፍያ እየተፈጸመ በመሆኑ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት እንዲጋለጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.8.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ማንኛውንም የሰራተኞች ጥቅማጥቅም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተፈቅዶ በኤጀንሲዉ ሲተላለፍ ብቻ ክፍያዉን ሊፈጽም ይኖርበታል፡፡ክፍያም ሲፈፅም መንግስት ባወጣቸው የአከፋፈል መመሪያዎች እና ህጎች መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡እንዲሁም ከላይ ያለአግባብ እየተከፈለ ያለው ክፍያ ከመመሪያ ውጭ በመሆኑ ሊስተካከል (ተመላሽ ሊደረግ) የሚገባው ሲሆን በ2009 በጀት ዓመት ያለአግባብ የተከፈለው ክፍያ ሙሉ በሙሉ ተሰልቶ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.8.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ዩንቨርስቲዉ ለህክምና ኮሌጅ መምህራን ከሚከፈለዉ ቶፕ አልዋንስ ጋር በተገናኘ መምህራኖቹ ለተግባር ትምህርት የዩኒቨርስቲያችን የህክምና ተማሪዎች በተለያዩ የህክምና ተቋማት ሲመደቡ መምህራኖቹ ከማስተማሩ ስራ ጎን ለጎን በሆስፒታሉ ወይም በህክናዉ ተቋም ዉስጥ የህክምና አገልግሎት ቢሰጡም ለማህበረሰቡ ያለዉ ፋይዳ የላቀ በመሆኑ በዚሁ መሰረት ለሚሰጡት የህክምና አገልግሎት ዩኒቨርስቲዉ አምኖበት በማኔጅመንት ቃለጉባኤ መሰርት እየከፈልን መሆኑን እያሳወቅን እንዲሁም የየኒቨርስቲዉ ተማሪዎች ታመዉ ወደዩኒቨርስቲዉ ክሊኒክ ለህክምና ሲመጡ የተሻለ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙና የጤና ተማሪዎችም ከቀላል ህክምና እስከ ከፍተኛ ህክምና ልምድ እንዲያገኙ በማሰብ መምህራኖቹም ከቋሚ ስራቸዉ ጎንለግን ማሰራት ስለተፈለገ በዩኒቨርስቱ ማኔጅመንት ቃለ-ጉባኤ መስረት የተከፈለ ክፍያ መሆኑን እናሳዉቃለን፡፡

3.9.1 ግኝት፣ ሕግና ደንብን ያልተከተለ ክፍያ፣

ከመደበኛ የሚፈፀሙ ክፍያዎች ደንብና መመሪያን የጠበቁ ለመሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ስናከናውን፣በናሙና ከታዩት ዉስጥ በድምሩ ብር 419,754.99 ልዩ ልዩ አገልግሎት ለሰጡት፣ለግቢ የውበት ስራ ለሰሩት፣ወንበር ለጠገኑት፣ሞጁል ያዘጋጁት በሚል ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ከመደበኛ በጀት ላይ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፡፡ የሂሳብ ዝርዝር እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 568344 በቀን 03/04/2009 ብር 144,000.00 ክፍያ የተፈጸመዉ ለስድስት የዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች የግቢዉን የዉበት ስራ ለሰሩት በሚል ለያንዳንዳቸዉ ብር 24,000.00(ለመሚህር አብረሃም ሙላቱ ብር 24,000.00፣ለመሚህር አክሎክ ዘዉዱ ብር 24,000.00፣ለመሚህር ታደለ አየለ ብር 24,000.00፣ለአቶ ሰንበት ነስሩ ከግቢ ጽዳትና ዉበት ክፍል ብር 24,000.00፣ለጀማል መሃመድ ከግቢ ጽዳትና ዉበት ክፍል ብር 24,000.00 እና ለአቶ በረከት ወልደ ከግንባታ ጽ/ቤት ብር 24,000.00) በድምሩ ብር 144,000.00 ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ከመደበኛ በጀት ላይ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፡፡
- ዩኒቨርሲቲው በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 568320 በቀን 02/03/2009 ብር 4,764.99 ክፍያ የተፈጸመዉ ለሶስት የዩኒቨርሲቲ መሚህራኖች ወንበር ለጠገኑት በሚል ለያንዳንዳቸዉ ብር 1,588.33(ለመለሰ ባዴ ብር 1,588.33፣ለአይተነዉ አበበ ብር 1,588.33 እና ለታከለ ዱባለ ብር 1,588.33) በድምሩ ብር 4,764.99 ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ከመደበኛ በጀት ላይ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፡፡
- ዩኒቨርሲቲው በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 283594 በቀን 28/04/2009 ብር 78,180.00 በተከታታይና ርቀት ት/ት ፕሮግራም በርቀት የሚወስዱ የት/ት ዓይነቶች ሞጁል ያዘጋጁ በሚል ለ9 መሚህራኖች አንድ ገጽ በብር 60.00 አጠቃላይ ገጽ 1,303.00*ብር 60.00=ብር 78,180.00 የሚመለከተዉ አካል ተመኑን ሳያጸድቅ ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ከመደበኛ በጀት ላይ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፡፡
- ዩኒቨርሲቲው በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 987527 በቀን 28/03/2009 ብር 110,520.00 በተከታታይና ርቀት ት/ት ፕሮግራም በርቀት የሚወስዱ

የት/ት ዓይነቶች ሞጁል ያዘጋጁ በሚል ለ11 መሚህራኖች አንድ ገጽ በብር 60.00 አጠቃላይ ገጽ 1,842.00*ብር 60.00=ብር 110,520.00 የሚመለከተዉ አካል ተመኑን ሳያጸድቅ ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ከመደበኛ በጀት ላይ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፡፡

- ዩኒቨርሲቲው በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 569029 በቀን 12/04/2009 ብር 59,890.00 በተከታታይና ርቀት ት/ት ፕሮግራም በክረምት መርሀ ግብር ለሚማሩ ተማሪዎች ሞጁል ያዘጋጁት በሚል ለ6 መሚህራኖች አንድ ገጽ በብር 60.00 አጠቃላይ ገጽ 997.00 *ብር 60.00=ብር 59,890.00 የሚመለከተዉ አካል ተመኑን ሳያጸድቅ ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ከመደበኛ በጀት ላይ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፡፡
- ዩኒቨርሲቲው በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 283594 በቀን 28/04/2009 ብር 12,800.00 ክፍያ የተፈጸመዉ ለቡታጅራ ቴክኒክና ስልጠና ኮሌጅ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለሰጡት በሚል ለ12 ሰራተኞች ለያንዳዳቸዉ በወር ለ2 ሰራተኞች ብር 500.00፣ለ2 ሰራተኞች ብር 400.00፣ለ1 ሰራተኛ ብር 300.00፣ለ1 ሰራተኛ ብር 200.00፣ለ6 ሰራተኞች ብር 150.00 በድምሩ የ4 ወር ብር 12,800.00 ከህግ፣ ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ከመደበኛ በጀት ላይ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፡፡
- ዩኒቨርሲቲው በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 282195 በቀን 28/08/2009 ብር 9,600.00 ክፍያ የተፈጸመዉ ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በቡታጅራ ካምፓስ ለማስተባበርና ለመደገፍ ለተወከሉ አካላት ክፍያ በሚል ለ10 ሰራተኞች ለያንዳ ዳቸዉ በወር ለ2 ሰራተኞች ብር 500.00፣ለ1 ሰራተኛ ብር 300.00፣ለ1 ሰራተኛ ብር 200.00፣ለ6 ሰራተኞች ብር 150.00 በድምሩ የ4 ወር ብር 9,600.00 ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ከመደበኛ በጀት ላይ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፡፡

3.9.2 ስጋት፣

- ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ ባልታወቀ የክፍያ ተመን ክፍያ መፈፀም የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ከመደረጉም በላይ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- መንግስት ለከፈለዉ ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ላያገኝ ይችላል፡፡

- ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ መፈጸም ግለሰቦች ያለአግባብ ተጠቃሚ ከማረጉም በላይ መንግስትን ለክሳራ ሊዳርግ ይችላል፡፡

3.9.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ያለአግባብ ከህግ፣ደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለዉ ገንዘብ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡እንዲሁም በ2009 በጀት ዓመት የተከፈሉ ተመሳሳይ ክፍያዎች ሙሉ በሙሉ ተሰልቶ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የዩኒቨርሲቲዉ ስራ አመራር ማንኛዉም ክፍያ በህግና ደንብ መሰረት ብቻ እንዲከፈል ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.9.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በወቅቱ ግቢዉን የማስዋብ ስራ መስራት መስራት ስፈላጊና ተገቢ የነበረ ቢሆንም ይህንን ሥራ የሚሰራልን አካል ለማግኘት ጫረታ ከማዉጣታችን በፊት ያለሰነድ ጥናት አድርግን የተገለጸልን ዋጋ አሁን ከከፈልነዉ ዋጋ አራት አጥፍ ሆኖ ስላገኘነዉ በእኛዉ መምህራኖች ብንጠቀም የተሻለ መሆኑን አምነንበት የተጸመ ክፍያ መሆኑን እየገለጽን በተሰጠዉ አስተያየት መሰረት የምናስመልስ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3.10.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ያለዉድድር የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ 2002 መሰረት አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 15/2 እና 15/3 በአዋጁ እና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፣የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ ተመስርቶ እንደሚከናወን ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣዉ ክፍል 8 አንቀጽ 31/1 የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን የግዥ አፈጻጸም ስርዓቶች ሊጠብቅ ያልቻለ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 5 በተደነገገዉ መሰረት ለኤጀንሲዉ ጥያቀያቸዉን አቅርበዉ ሲፈቀድላቸዉ ብቻ ነዉ በማለት ደንግጓል፡፡ እንዲሁም የዴፌራል መንግስት ግዥ መመሪያ አንቀጽ 25(7) ሀ ላይ የመንግስት መ/ቤት በግዥ እቅድ ዉስጥ ያላካተቱ ዋጋቸዉ እስከ ብር 5,000.00 ያልበለጠ እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር ተያይዞ

የቀጥታ ግዥዎችን ከማናቸዉ ሻጭ ድርጅት መፈጸም እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ እንደሂሁም በፌዴራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት ዕቃው፣የግንባታ ዘርፍ ስራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ስረጋገጥ ነዉ ብሎ ይደነግጋል፡፡ ዩኒቨርሲቲዉ የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥን ከላይ በተጠቀሱት አዋጅ እና መመሪያ መሰረት እያከናወነ መሆኑን ኦዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርስቲው በተለያየ ጊዜ ያለምንም ውድድር በድምር የብር 1,507,994.06 የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ በራሱ በማዘዝ በቀጥታ ከየጆካ ሆቴል፣ ፍቃዱ አሰሬ (ከፋ ሆቴል) እና እኒተርኮንተነታል አዲስ ሆቴል ግዥ ተፈጽሞ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ግዥ ሲፈጽም ንግድ ፍቃድ አውጥቶው በዘርፉ የተሰማሩ አለመኖራቸውን ሳያረጋግጥ ወይም ብቸኛ አቅራቢ መሆኑን ከሚመለከተዉ አካል መረጋገጫ ሳይሰጥ በቀጥታ በማዘዝ ግዥ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሂሳብ ዝርዝርም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁ	ቀን	የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር	ወጪውን ያዘዘው ባለሥልጣን	ገንዘቡን የተቀበለው ሰው(ድርጅት) ስም	የወጪው ምክንያት	የተከፈለው የገንዘብ ልክ
1	20/03/09	568334	ፍቃዱ ሲማ	የጆካ ሆቴል	በተለያዩ ጊዘ ወደ ዩኒቨርስቲዉ ለሚመጡ እንግዶች ለመስተንግዶ የተከፈለ ወጪ ለተደረገበት የተከፈለ	97,027.38
2	15/09/09	982932	ፍቃዱ ሲማ	ከፋ ሆቴል	ከወልቂጤ ዩኒቨሲቲ ለመጡ መምህራን የመስተንግዶ አገለግሎት የሰጡበት የተከፈለ ወጪ	279,054.00
3	26/10/09	570343	ፍቃዱ ሲማ	Intercontinent al Addis Hotel	ዩኒቨርስቲዉ ባዘጋጀዉ አምስተኛዉ አለም አቀፍ የCSR ኮንፈርንስ ለተሳታፍዎች የመስተንግዶ አገልግሎት ክፍያ	784,097.00
4	07/07/09	569284	ፍቃዱ ሲማ	የጆካ ሆቴል	የእንግዶች መስተንግዶ የተደረገበት ክፍያ	347,815.68
					ድምር	**1,507,994.06**

3.10.2 ስጋት፣

- ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ይህም ቁጠባን ፣የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፣
- የመንግሥትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- ማንኛዉም ግዥ የግዥ መመሪያ ተከትሎ አለመፈፀም ተጠያቅነት ከማስከተሉም በላይ ለመንግስት ገንዘብ ሚዝበራ መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

3.10.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ዩኒቨርሲቲው የመንግሥትን ገንዘብ ከብክነት እና ከምዝበራ ለመከላከል ማንኛውም ግዥ መፈፀም ያለበት መንግሥት ባወጣው የግዥ ስርዓት መሆን ይኖርበታል፡፡
- ዩኒቨርሲቲዉ አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑን የሚገልጽ መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡መረጃ ሳይኖር አገልግሎቱ የሚገኘዉ ከአንድ ድርጅት ብቻ ነዉ በማለት ከአንድ ድርጅት ያለዉድድር ግዥ መፈጸም የመንግስትን ገንዘብ ለሚዝበራ እንደሚያገልጥና ተጠያቅነትን እንደሚያስከትል የዩንቨርሲቲዉ ስራ አመራር አዉቆ ለመስተንግዶ አገልግሎት ንግድ ፍቃድ ያወጡትን አወዳድሮ ግዥ እንድፈጸም ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ሌሎች ድርጅቶች በዘርፉ ተሰማርቶ በመንግስት አገልግሎቱን መስጠት ይችላሉ ተብሎ ንግድ ፍቃድ የተሰጣቸዉ ለመንግስት ግብር የሚከፍሉት ሁሉ መወዳደር ይኖርበታል፡፡ የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥም ዉድድርን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

3.10.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ያለጨረታ /ውድድር/ ስለተፈፀመ የአገልግሎት ክፍያዎች በተመለከተ ብር 1,507,994.06 ለጃካ፤ ለፍቃዱ አሶሬና ለኢንተር ኮንቴነታል ሆቴሎች ለሰጡት የመስተንግዶ አገልግሎት ሥለተከፈለዉ ክፍያ በተመለከተ ወደፊት ለሚገጥሙን የመስተንግዶ ወጪዎች ግዢ አጀንሲ በማስፈቀድና ከላይ በተራ ቁጥር 3 ቡሌት 4 በሰጠነዉ አስተያየት መሰረት የረሳችን የማወዳደሪያ መስፈርት አውጥተን በማወዳደር ግዢ የምንፈጽም መሆንን እንገልጻለን፡፡

3.11.1 ግኝት፣ ያለ ግልፅ ጨረታ የሃይላንድ ዉሃ ግዥ፣

በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ

ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ ተመስርቶ እንደሚከናወን ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣዉ ክፍል 8 አንቀጽ 31/1 የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን የግዥ አፈጻጸም ስርዓቶች ሊጠብቅ ያልቻለ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 5 በተደነገገዉ መሰረት ለኤጀንሲዉ ጥያቀያቸዉን አቅርበዉ ሲፈቀድላቸዉ ብቻ ነዉ በማለት ደንግጓል፡፡ እንዲሁም የዴፌራል መንግስት ግዥ መመሪያ አንቀጽ 25(7) ሀ ላይ የመንግስት መ/ቤት በግዥ እቅድ ዉስጥ ያላካተቱ ዋጋቸዉ እስከ ብር 5,000.00 ያልበለጠ እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር ተያይዞ የቀጥታ ግዥዎችን ከማናቸዉ ሻጭ ድርጅት መፈጸም እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ዩኒቨርሲቲዉ የሃይላንድ ዉሃ እስከ ብር 5,000.00 ብቻ በቀጥታ ግዥ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከብር **5,000.00 በላይ** የብር **429,986.96** የሃይላንድ ዉኃ ግዥ በአንድ ጊዜ ያለጨረታ(ያለምንም ዉድድር) በቀጥታ ከኤደን ቢዝነስ አ.ማ ግዥ ተፈጽሞ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሂሳብ ዝርዝርም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 882831 በቀን 17/02/2009 ብር 429,986.96 የሀይላንድ ዉሃ ግዥ ከኤደን ቢዝነስ አ.ማ ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተከፈለ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.11.2 ስጋት፣

- ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ይህም ቁጠባን ፣የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፣
- የመንግሥት ለከፈለዉ ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ላያገኝ ይችላል፡፡
- ማንኛዉም ግዥ የግዥ መመሪያ ተከትሎ አለመፈፀም ተጠያቅነት ከማስከተሉም በላይ ለመንግስት ገንዘብ ሚዝበራ መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

3.11.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው የመንግሥትን ገንዘብ ከብክነት እና ከምዝበራ ለመከላከል ማንኛውም ግዥ መፈፀም ያለበት መንግሥት ባወጣው የግዥ ስርዓት መሆን ይኖርበታል፡፡

3.11.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ያለውድድር በብር 429,986.96 ስለተገዛው እሽግ ውሃ በተመለከተ፡- የተማሪዎች አገራዊ ስልጠና እንድንሰጥ በአጭር ጊዜ ስላሳወቁን የማወዳደሪያ ጊዜ በቂ ስላንነበር አገልግሎቱ አካባቢው ካሉ ሆቴሎች ለመግዛት ዋጋው ከፍተኛ በመሆኑና ከነበረው የጊዜ እጥረት አንፃር የተሻለ የመንግስት ጥቅም ያስጠብቃል ብለን ባሰብነውና ነጋዴዎች ከሚሸጡበት ዋጋ የ0.5 ሊትር እሽግ ውሃ እስከ 3 ብር ቅናሽ ባለው ዋጋ ፋብሪካው በሚያከፋፍልበት ዋጋ እንዲሠጠን በመስማማት በማኔጅመንት ውሳኔ መሰረት ግዥው የተፈፀመ ሲሆን ከዚህ በኋላ ተመሳሳይ ክፍተት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ እናደርጋለን፡፡

3.12.1 ግኝት፣ ለኃላፊዎችና ለአስተዳደር ሠራተኞች ያለአግባብ ሳይፈቀድ የተከፈለ፣

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ 30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ በሥራ አመራር ቦርድ የሚመሩ አንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሰራተኞችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለሥራ አመራር ቦርድ እያቀረቡ በማስወሰን ተግባራዊ ማድረጋቸዉን ገልጾ ይህ ጉዳይ የሚንስትሮች ምክርቤት በ4ኛዉ የምርጫ ዘመን 15ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ተነስቶ ዉይይት ከተደረገበት ቦኃላ "ከጠቅላይ ሚኒስተር ጽ/ቤት እዉቅናና ፈቃድ ዉጭ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ/በቦርድ/የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስካሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች ባስቸኳይ እንዲቋረጡ" መመሪያ አስተላልፏል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ከመደበኛ በጀት የሚከፈለው ጥቅማጥቅሞች ሲታይ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የርቀትና ተከታታይ ትምህርትን ስራ ጋር ልዩ ልዩ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ላስተባበሩት በሚል በየደረጃቸዉ በተለያየ የክፍያ ተመን ከመደበኛ ሂሳብ የሚከፈል ሲሆን በናሙና ከታየዉ ዉስጥ በድምሩ ብር 694,717.78 ከመደበኛ በጀት ላይ ያለአግባብ ሳይፈቀድ ተከፈሎ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ እደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የሂሳብ ምዝገባ ማዘገቦ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	ተከፈለ	የገንዘቡ ልክ
1	28/03/2009	987527	በተከታታይ ርቀት ት/ት ፕሮግራም ልዩ ልዩ አገልግሎት ለሰጡ የአስተዳደር	ለ62 ሰራተኞች	404,090.28

			ሰራተኞች ክፍያ		
2	28/10/2009	173052	በተከታታይ ርቀት ት/ት ፕሮግራም ልዩ ልዩ አገልግሎት ለሰጡ የአስተዳደር ሰራተኞች ክፍያ	ለ52 ሰራተኞች	290,627.50
ድምር					**694,717.78**

3.12.2 <u>ስጋት፣</u>

- በመመሪያ ያልተደገፈ ክፍያ መፈጸም ለመንግስት ገንዘብ ምዝበራ መንስኤ ከመሆኑም በላይ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በሚመለከተዉ አካል ያልጸደቀ ጥቅማጥቅም የክፍያዉ ትክክለኝነት ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

3.12.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ በጀት የሚከፈል ጥቅማጥቅም በሚመለከተዉ አካል ተፈቅዶ ሲተላለፍ ብቻ ክፍያዉን ሊፈጽም ይኖርበታል፡፡ ክፍያም ሲፈፅም መንግስት ባወጣቸው የአከፋፈል መመሪያዎች እና ህጎች መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ከላይ ያለአግባብ እየተከፈለ ያለው ክፍያ ከመመሪያ ውጭ በመሆኑ ሊስተካከል (ተመላሽ ሊደረግ) የሚገባው ሲሆን በ2009 በጀት ዓመት ያለአግባብ የተከፈለው ክፍያ ሙሉ በሙሉ ተሰልቶ ተመላሽ ሊደረግና ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.12.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የርቀትና ተከታታይ ትምህርት ላስተባበሩ የተለያዩ ሀላፊዎች አስተባባሪዎች ስለተከፈለው 669,4717.78 በተመለከተ ምንም እንኳን ችግሩ የውስጥ ገቢ እና የመደበኛ በጀት ለያይተን ባለመመዝገባችን ምክንያት የተፈጠረ ቸግር ቢሆንም ከአሁን በኋላ በተሰጠን አስተያየት መሰረት በቦርድ አጸድቀን ክፍያዉ ከውስጥ ገቢ ቢቻ የምንፈጽም መሆኑን፡፡

3.13.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከዉስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ ሳይፈቀድ ለመደበኛ ስራ ለተማሪዎች ቀለብ የተከፈለ፣</u>

የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ እንደሆነ ያዛል፡፡በዚህ መመሪያ መሰረት

ከዉስጥ ገቢ በጀት ለመደበኛ ስራ የተፈፀሙ ክፍያዎች በመንግስት የተፈቀደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርሲቲዉ ከውስጥ ገቢ ለመደበኛ ስራ ለተማሪዎች ቀለብ እንዲጠቀም በመንግስት የተፈቀደ ሳይኖር በናሙና ከተየዉ ዉስጥ በድምሩ ብር 712,781.52 ለመደበኛ ስራ ለተማሪዎች ቀለብ ያለአግባብ ከዉስጥ ገቢ በጀት ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ወጪውም ከዉስጥ ገቢ በጀት ላይ ወጪ ሆኖ እያለ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ከመደበኛ በጀት ላይ ወጪ እንደተደረገ ተደርጎ በፋይናንስ ምንጭ 1800 ያለአግባብ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሂሳብ ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የገንዘብ መጠን	የወጪዉ ሚክንያት
1	25/09/09	570311	207,881.52	ለተማሪዎች ቀለብ
2	28/10/09	187855	504,900.00	ለነን-ከፊ ተማሪዎች
ድምር			712,781.52	

3.13.2 ስጋት፣

- ዩኒቨርሲቲዉ መንግስት ለመደበኛ ስራ ከሚመድበዉ በጀት ዉጪ ከዉስጥ ገቢ ሳያስፈቅድ የሚጠቀም ከሆነ ለመንግስት ገንዘብ ሚዝበራ መንስኤ ከመሆኑም በላይ ተጠያቅነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ዩኒቨርሲቲዉ ከዉስጥ ገቢ በጀት ላይ ለመደበኛ ስራ በሚመለከተዉ አካል ሳይፈቀድ የሚጠቀም ከሆነ በጀቱ ያለአግባብ ላልታለመለት አላማ ሊዉል ይችላል፡፡

3.13.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

መንግስት ከዉስጥ ገቢ በጀት ላይ ለተማሪዎች ቀለብ ዩኒቨርሲቲዉ እንዲጠቀም ሲታወጀለት የተወጀለተት መጠን ብቻ ከዉስጥ ገቢ በጀት ላይ አዉጥቶ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ለወደፊቱም የዩኒቨርሲቲዉ ስራ አመራር የዉስጥ ገቢ በጀትን አጠቃቀምን በተመለከተ በፋይናንስ ሕግና ደምብ መሰረት እንዲሆን ጥብቅ ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡

3.13.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በዋጋ ንረት ምክንያት ለዓመቱ የተያዘው የተማሪዎች ቀለብ በጀት በቂ ስላልነበረና በዚህ ምክንያት የምግብ አቅርቦት ላይ በጥራትና በመጠን ማነስ ምክንያት የመማር ማስተማር ስራው እንዳይደናቀፍ ለማድረግ ከውስጥ ገቢ በዩኒቨርሲቲው ቦርድ አመራር በማፀደቅ

ክፍያ የፈፀምን ሲሆን በቀጣይ ከመደበኛ በጀት አብቃቅተን ለመጠቀም ጥረት እናደርጋለን፡፡

3.14.1 ግኝት፣የሂሳብ መደቡን ያልጠበቁ ወጪዎች፣

የፌዴራል መንግስት መስራ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 7 ፊደል ሀ የመንግስት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በሥራ ክፍል ወይም በፕሮጀክት፣በፋይናንስ ምንጭ እና በየወጪ የሂሣብ መደቡ የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር ከፍተው እንቅስቃሴውን መመዝገብና መቆጣጠር እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚህም መሰረት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ አያያዝ ኦዲት ሲደረግ፣

- በድምሩ ብር 1,034,508.00 በተገቢው ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ወጪዉ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ቢሆን በሂሳብ መደብ 6231 ብር 4,248,549.56፣ በሂሳብ መደብ 6251 ብር 3,654,283.18 ከበጀት በላይ የተጠቀሙ መሆኑን የሚያመለክት ስለመሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቀ	ቀን	የወጪ dስመ ስከሪያ ቁጥር	በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ	የወጪ ምክንያት	መመዝገብ የነበረበት ሂሳብ መደብ	የገነዘቡ መጠን
1	8/05/09	989168	6231	ለስልጠና	6271	93,680.00
2	30/01/09	987658	6231	ለትራንስፖርት	6232	1,652.00
3	27/01/09	882773	6231	ለትራንስፖርት	6232	676.00
4	07/02/09	568754	6271	የተማሪዎች ዉሎ አበል	6231	88,500.00
5	03/08/09	0846365	6314	ለተማሪዎች ምግብ ቤት በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት በገቡት ውል መሠረት አገልግሎት ለተሰጠበት	6251	850,000.00
ድምር						**1,034,508.00**

3.14.2 ስጋት፣

የወጪው በጀት ላይ አሉታው ተፅኖ ከማድረሱም በላይ የመንግስት የፋይናንስ የሂሳብ አያያዝ ይጥሳል፡፡

3.14.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ዩኒቨርሲቲው ማንኛውንም ክፍያ ሲፈፅም በተገቢው የወጪ መደብ አርዕስት ወጪ ሆኖ እና ተመዝግቦ ሪፖርት ካልተደረገ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ከማድረጉም በተጨማሪ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ በመሆኑ ለተፈጠረው ስህተት ተገቢውን ማስተካከያ መደረግ እንዳለበት እና ለወደፊቱ ምዝገባ በሚከናወንበት ወቅት ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

3.14.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

ከወጪ የሂሳብ መደብ አመዘጋገብ የተፈጠረው ክፍተት ከባለሙያው የግንዛቤ ጉድለት የተነሳ በስህተት የተመዘገበ ስለሆነ በቀጣይ ስልጠና ለባለሙያ በማመቻቸትና የሰው ሀይል በመመደብ በጥንቃቄ እንመዘግባለን።

3.15.1 **ግኝት፣ ባለ 5 ፎቅ የመምህራን መኖርያ እና የእንግዳ ማረፊያ ህንጻ የዲዛይን አገልግሎት ያለጨረታ ግዥ የተፈጸመ፣**

በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፣የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ ተመስርቶ እንደሚከናወን ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣዉ ክፍል 8 አንቀጽ 31/1 የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን የግዥ አፈጻጸም ስርዓቶች ሊጠብቅ ያልቻለ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 5 በተደነገገዉ መሰረት ለኤጀንሲዉ ጥያቀያቸዉን አቅርበዉ ሲፈቀድላቸዉ ብቻ ነዉ በማለት ደንግጓል። እንደሂሁም በፌዴራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት ዕቃው፣የግንባታ ዘርፍ ስራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ስረጋገጥ ነዉ ብሎ ይደነግጋል። በዚህ የግዥ አዋጁ መሠረት በናሙና ኦዲት ለማድረግ ሲሞከር የብር 2,584,660.44 የዲዛይን አገልግሎት ያለጨረታ(ያለዉድድር) ግዥዉ ከአንድ ድርጅት

በቀጥታ ተፈጽሞ የተከፈለ መሆኑን ይሁን እንጅ ዩኒቨርሲቲዉ ግዥ ሲፈጽም ንግድ ፍቃድ አዉጥቶ በዘርፉ የተሰማሩ አለመኖራቸዉን ሳያረጋግጥ ወይም ብቸኛ አቅራብ መሆኑን ከሚመለከተዉ አካል መረጋገጫ ሳይሰጥ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን የህንጻና ከተማ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ዘርፍ ያለዉድድር በቀጥታ ግዥዉ ተፈጽመ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሂሳብ ዝርዝሩም እንደምከተለዉ ቀርቧል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0846375 በቀን 26/08/2009 ብር 2,584,660.44 ባለ 5 ፎቅ የመምህራን መኖርያ ቤት እና የእንግዳ ማረፊያ ህንጻ ዲዛይን የአገልግሎት ግዥ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን የህንጻና ከተማ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ዘርፍ ያለጨረታ (ያለዉድድር) በቀጥታ ግዥዉ ተፈጽሞ የተከፈለ መሆኑን፣

3.15.2 <u>ስጋት፣</u>

- ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ይህም ቁጠባን፣የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡
- የመንግሥትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.15.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ግዥ በመመሪያው መሠረት ስለመፈጸሙ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም የመንግስትን ገንዘብ ያለአግባብ ወጪ ለመከላከል እና ለመስሪያ ቤቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያስገኝ በዘርፉ የተሰማሩ በርካታ ድርጅቶች በመኖራቸው ግዥ በግዥ መመሪያው መሰረት ሊፈፀም ይገባል፡፡

3.15.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐር ቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን የህንፃና ከተማ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ዘርፍ መንግስታዊ የልማት ድርጅት መሆኑ ታሳቢ በማድረግ ካላቸው መልካም ስምና ስራ አፈፃፀም መነሻ በማድረግ ከነበረብን የመምህራን የመኖሪያ ቤት እጥረት የመኖራ ቤት ጥያቄ ዉጥረት ምክንያት የተፈጠረው የመምህራን ፍልሰት ለመከላከል በአጭር ጊዜ ውስጥ ጨረታ አውጥተን ለማወዳደር የሚወስደውን ጊዜ ለመቀነስ ሲባል በማኔጅመንት ውሳኔ የአገልግሎት ግዥው የተፈፀመ ሲሆን በቀጣይ ተመሳሳይ ክፍተት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ እናደርጋለን፡፡

4. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

4.1 ግኝት፣ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ የሚሰበሰብ ወይም የሚወራረድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በ2009 በበጀት ዓመት መጨረሻ ከሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በድምሩ ብር **3,958,759.50** ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ተራ ቁ.	ተሰብሳቢው የቆየበት	የገንዘቡ መጠን
1	ከ5 ዓመት በላይ	0.00
2	ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	3,901,072.14
3	ከወር እስከ 1 ዓመት	77,687.36
ድምር		3,958,759.50

(ለዝርዝሩም አባሪ 4 ተያይዟል)

- በሂሳብ መደብ 4251 ለስራ ተቋራጮች የተያዘ የተሰብሳባ ሂሳብ ለያንዳንዱ ስራ ተቋራጮች የተከፈተ ተቀጽላ ሌጀር የሌለው በመሆኑ ለኦዲት ስራ አስቸጋር ሆኖ የተገኘ መሆኑን፡፡

4.2 ስጋት፣

- የመንግስትን ገንዘብ በወቅቱ አለመሰብሰብ ለገንዘብ ጥፋትና ብክነት መንስዔ ሊሆን ይችላል፡፡
- በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረድ ቁጥጥር ካልተደረገ ለውዝፍ ሰነድ ክምችት መንስዔ ሊሆን ይችላል፡፡
- ተሰብስቦ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ውስን ሀብት /ገንዘብ/ ያለሥራ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በውዝፍ የሚገኘው ተሰብሳቢ ሂሳብ በአፋጣኝ እንዲወራረድ፣ለድርጅቶች እና ለግለሰቦች የተሰጠው ብድር በአፋጣኝ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ለወደፊቱም ቅድሚያ ክፍያዎች በደንቡ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረዱ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

4.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- ✓ በተሰብሳቢ ተመዝግቦ የሚገኘው ብር 3,958,759.50 አብዛኛው ከግንባታ ፕሮጀክት ጋር የተያያዙ ሂሳቦች ስለሆኑ ከግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀት መሰብሰብ የሚችሉትን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲሰበሰቡ የምናደርግ ሲሆን መሰብሰብ ያልቻሉትን በእድሜ ዘመን ለይተን ለማኔጅመንቱ አቅርበን በማስወሰን ለሚመለከተው አካል የምናሳውቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ✓ ተቀጽላ ሌጀር በተመለከተ በክፍሉ በቂ የሂሳብ ባለሙያ ባለመኖሩ ምክንያት የተፈጠረ ክፍተት ሲሆን ከያዝነው በጀት ዓመት ጀምሮ በእያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ ስም ተቀጽላ ሌጀር ከፍተን ለመመዝገብ መዘጋጀታችን እንገልጻለን፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ፣

5.1 ግኝት፣ በወቅቱ ያልተከፈለ (ያልተወራረደ) ተከፋይ ሂሳብ፣

የዩኒቨርሲቲው የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ የሚከፈል ወይም የሚወራረድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ከሚታይ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በድምሩ ብር **2,428,472.51** ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

ተራ ቁ.	ተከፋይ የቆየበት	የገንዘቡ መጠን
1	ከ5 ዓመት በላይ	0.00
2	ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	2,272,529.09
3	ከወር እስከ 1 ዓመት	155,943.42
ድምር		2,428,472.51

ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ገንዘቡ ገንዘቡ በተከፋይ የተያዘበት ቀን፣ወር እና ዓ.ም	ሂሳብ መደብ	ገንዘቡ የሚከፈልለት ግለሰብ(ድርጅት)ስም	የሚከፈለዉ ገንዘብ መጠን
1	30/10/2008	**5001**	ቃሊቲ ኮንስትራክሽን	1,050,865.54
2	30/9/2008	**5002**	ዘላለም(ይረጋለም) ኮንስትራክሽን	980,529.68
3	30/9/2008	“ “	ዛምናእና ኤክስፐረስ	27,600.00
4	25/12/2007	“ “	ለይላ አህምደ አስመጪ	63,244.00
5	5/12/2007	“ “	አስማማው	6,125.00

6	30/9/2008	“ “	የወልቂጤ/ዩንቨርስቲ ሸማቾች ማህበር	102,762.32
7	1/8/2008	“ “	ባነር ቴክኖ	41,402.55
8	28/10/2009	**5003**	የጡረታ ሚኒስቴር	130,404.10
9	30/10/2009	**5028**	ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር	25,539.32
			ድምር	**2,428,472.51**

5.2 ስጋት፣

ዕዳ በጀት ዓመቱ ሳይከፈል ቀርቶ ለሚቀጥለዉ በጀት ዓመት ዞሮ መከፈሉ በበጀት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር፣ እና ያለ ሥራ የተቀመጠውን ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ተከፋይ እዳዎች ለተቋሙ ጥቅም የዋሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል በበቂ ማስረጃ ተደግፎ እንዲያዝና በወቅቱ እንዲከፈል የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በተከፋይነት የተመዘገበው 2,428,472.51 ለረጅም ጊዜ ሲንከባለል የመጣና አቅራቢዎች ቀርበው ክፍያ ባለመጠየቃቸው ሳይከፈል የቆየ ሲሆን ይህ ክምችት ለመቀነስ ከአቅራቢዎች ከተከፋይ አካለት ጋር ተነጋግረን እልባት የምንሰጠዉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

6. የበጀት ሂሣብ፣

6.1 ግኝት፣

ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት ከተፈቀደው፡-

- ለመደበኛ(1800) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 4,700,071.38 ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን፣ብር 15,773,733.19 ደግሞ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ መሆኑን፣
- ከዉስጥ ገቢ(1900) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 1,663.56 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ መሆኑን፣

- ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው ወጪ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 139,379,026.28 ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን፣ብር 980,183.78 ደግሞ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ መሆኑን በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡ ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል፡፡

6.2 <u>ስጋት፣</u>

- ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት ባለመጠቀሙ ሊደርስበት ካቀደው ግብ ላይደርስ ይችላል፡፡ ሌሎች መ/ቤቶች ሊጠቀሙበት የሚችሉት ውስን ሀብት /በጀት/ ያለጥቅም እንዲቀመጥም ያደርጋል፡፡
- በሌላ በኩል ደግሞ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ክፍያ የሚፈጸመው ወይም ወጪ የሚደረገው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ እንደሆነ የተደነገገ በመሆኑ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ መንግስት ለተጨማሪ ወጪ ግዴታ ውስጥ ሊገባም ይችላል፡፡

6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ዩኒቨርሲቲው የበጀት አጠቃቀሙን በተመለከተ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውንም የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡
- ማናቸውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት አስቀድሞ የተፈቀደ ወይም በዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ የተስተካከለ በቂ በጀት ለመኖሩ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

6.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- ✓ ስራ ላይ ያልዋለው በጀት ብር 4,700,071.38 በተመለከተ፡- አቅራቢዎች በሀገሪቱ በተፈጠረው የዶላር ምንዛሬ እጥረት ምክንያት በውላቸው መሰረት ማቅረብ ባለመቻላቸው የተፈጠረ ችግር ነው፡፡ ከበጀት በላይ የተጠቀምነው ደግሞ በገበያ ዋጋ ንረት ምክንት የተፈጠረ ችግር ነው፡፡
- ✓ ከውስጥ ገቢ ጋር በተገናኘ ከበጀት በላይ የተጠቀምነው ብር 1,663.56 ከላይ እንደተገለፀው በገበያ ዋጋ ንረት ምክንያት የተፈጠረ ችግር ነው፡፡
- ✓ ከካፒታል ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ ሥራ ላይ እንዳልዋለ ስለተገለታ ገንዘብ በር 139379026.28 ምክንያት ገንዘቡ በ2009 በጀት አመት ለጀመርናቸዉ የመምህራን መኖሪያ ቤቶችን ለሆስፒታል ግንበታዎች አቅድመ ክፍያ የከፈልነዉ በመሆኑ

በተሰብሳቢነት የተመዘገበ በመሆኑ ሲሆን ይህም በዋጋ ንረት ምክንያት የተፈጠረ ክፍተት መሆኑን ታወቆ ወደፊት ተገቢዉን ጥንቃቄ የምናደርግ መሆኑን እንገጻለን፡፡

7. ንብረት፣

7.1 ግኝት፣ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች፣

የዩንቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፣አጠቃቀምና አስተዳደር በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- የቋም ንብረቶች መለያ ቁጥር ሙሉ በሙሉ ያልተሰጠ መሆኑን፣
- በቋሚና በአላቅ ንብረት ክፍል (ስቶር) ውስጥ ንብረቶችን የመጠበቅ፣ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 ገቢና ወጪ የሚሰራ በአንድ ግለሰብ መሆኑን፣
- በኤሌክትሮኒክስ ንብረት መጋዘን ውስጥ አንድ ጄነሬተር በ2006 በጀት ዓመት ተገኝቶ የገባ ሲሆን ከ2006 ዓመት ጀምሮ ያለስራ በመቀመጡ ለብሊሽት እየተዳረገ መሆኑን፣
- ብዛታቸዉ 49 የሚሆን የሚወገዱ ላፕቶፖች በአላቅ ንብረት ክፍል ዉስጥ በአንድ ሮቶ ዉስጥ ተከማችቶ የተገኘ መሆኑን፣
- በአላቅ ንብረት መጋዘን ዉስጥ አንድ የማሽን ድስት የሚያገለግል የተቀመጠ መሆኑን፣
- በቋሚ ንብረት መጋዘን ዉስጥ የሚወገዱ ብዛታቸዉ 521 የመኪና ጎማ እና ብዛታቸዉ 34 የመኪና ባትር ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑን፣
- በተመላሽ ቋሚ ንብረት ክፍል በር አከባብ ሜዳ ላይ ብዛታቸዉ የማይታወቅ የሚወገዱ ፊራሽ፣ትራስ፣የብረት አልጋ እና ቹፐዶች ይወገዱ የተቀመጡ መሆኑን፣
- በተመላሽ ቋሚ ንብረት መጋዘን ዉስጥ ብዛት ያላቸዉ ንብረቶች ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት እና ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት የማይችሉት አንድ ላይ ተከማችቶ የተቀመጡ መሆኑን፣
- በቋሚ ንብረቶች የተጠቃም ካርድ (user card) ለተጠቃም አካል (ለሰራተኛዉ) ያልተሰጠ መሆኑን፣

- በተመላሽ ቋሚ ንብረት መጋዘን ዉስጥ በስጦታ መልክ የሚወገዱ የሚሰራ 391 ቺፑድ ፣555 የተማሪዎች አልጋ ባለ ችፑድን፣237 የአልጋ በወጣጫ መሰላል፣206 የተለያዩ የላብ ወንበሮች፣447 በከፊል የተጎዳ የተማሪዎች የመማሪያ ወንበር እና 781 የተማሪዎች ሎከር ተከማችቶ ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑን፣
- በአዲስ የሚሰራ የአስተዳደር ፅ/ቤት አከባብ እና በቋሚ ንብረት ተመላሽ ዉስጥ ሳይወገዱ የተቀመጡ ብዛታቸዉ 108 ፒላስትክ በርሜል፣2 የብረት ሽልፍ ፣383 ኤልክትሪክ ምጣድ፣15ኪግ ቁርጭራጭ ቆርቆሮ፣5 ሲንኪ፣1 ጋልቫናይዝድ ሼልፍ፣1 የብረት መሰላል፣17 ማንቆርቆሪያ ባለ 5 ሊትር፣21 የብረት ሳፋ፣8 ፕላስትክ ባልዲ ባላ 20 ሊትር፣13 ካስታ፣29 ጉርድ የብረት በርሜል፣9 የብረት ወንፍት፣1 ሮቶ ባለ 1000ሊትር፣7 ሮቶ ባለ 500 ሊትር፣1 ትልቁ ድስት፣10 መደረደሪያ ያለቸዉ ብረት፣162 ፕላስትክ የዉሀ ማስተላለፊያ ቧንባዎች፣8 ፋይል ካብኔት፣1 ማሽን ካብኔት፣30 ብረት ምድጃ፣8 የብረት ጠረጴዛ ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑን፣
- በተመላሽ ቋሚ ንብረት ዉስጥ በማቃጠልና በመሰባበር የሚወገዱ ብዛታቸዉ 26 የላይብረሪ ጠረጴዛ፣761 የምግብ ቤት ወንበር፣333 የምግብ ቤት ጠረጴዛ፣6 L-shape table፣17 office table፣2 የላይብረሪ ወንበር፣2 የፀሀፊ ወንበር፣84 white boar፣;24 Green board፣1 ኬዝ ቦክስ፣185 ሎከር፣3 ፔንስል ሻርፒነር፣14 ሳይንቲፊክ ካልኩሌተር፣202 ዲቫይደር፣5 ሀይባክ ቼር፣8 ፓንቸር፣51 የተማርዎች ትራስ፣11 ፔፐር ትሪ፣3 ማስመሪያ 50c.m፣110 የቆሻሻ ቅርጫት፣27 እስቴፕለር፣1 ትልቁ መቀስ፣45 የእነጀራ ሰፌድ፣ 32 ቼፑድ፣ 49 ፍላሽ፣7 ሀርድ ዲስክ እና 1 wiles CDMA፣160 የተቃጠለ የብረት አልጋና 20 ኪግ ቁርጭራጭ ብረታ ብረቶች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

<u>**የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ ግምጃ ቤት፣**</u>

- በተማሪዎች ግምጃ ቤት ንብረት ክፍል ዉስጥ ቢን ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም ባአግባቡ በንብረት ላይ ያልተለጠፈ መሆኑን፣
- በተማሪዎች ግምጃ ቤት ንብረት መጋዘን (ስቶር) ክፍል ውስጥ የምግብ ጥሬ ዕቃ የመጠበቅ፣ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 ገቢና ወጪ የሚሰራ በአንድ ግለሰብ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

<u>የተማሪዎች ክሊኒክ፣</u>

- በመድሀኒት መጠበቂያ ግመጃ ቤት ክፍል ውስጥ ቢን ካርድና ስተክ ካሪድ ያልተቋቋመ መሆኑን፣
- የመድሀኒት መጠበቂያ (ስቶር) ክፍል ውስጥ መዳኒትቶችን የመጠበቅ፣ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 ገቢና ወጪ የሚሰራ በአንድ ግለሰብ መሆኑን፣
- የመድሀኒት መጠበቂያ (ስቶር) ክፍል ውስጥ ብዛት ያላቸው መድሃኒቶች፣ 23 መጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሀኒቶች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>የመኪና አያያዝና አጠቃቀም፣</u>

ትራክተሩ ታርጋ ቁጥር እና የተሽከርካሪዉን የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌለዉ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጦል፡፡

7.2 **<u>ስጋት፣</u>**

- ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግቦ ካልተጠበቁ ለጉዳት፣ ለዝርፊያ እና ለብክነት ይዳረጋሉ፡፡
- የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላው ተሽከርካሪ የዩኒቨርሲቲ ንብረት ስለመሆኑ ማረጋገጥ አያስችልም፣

7.3 **<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>**

- የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ከላይ በተዘረዘሩት የቁጥጥር ድክመቶችና የአሰራር ክፍተቶች ላይ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡
- የባለበትነት መታወቅያ ደብተር የለሌዉ ትራክተር በምመለከተዉ አካል የባለበትነት ደብተር አግኝቶዉ ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡
- ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች እንዲቀረፉና ለወደፊቱም እንዲስተካከሉ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

7.4 **<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>**

- ✓ ቀደም ሲል የቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም አሰራሩን ይበልጥ በማዘመንና በቴክኖሊጂ ለመደገፍ ከአይሲቲ ዳይሬክቶሬት ጋር በመወያየት ሶፍት ዌር የማደራጀት ስራ እየተጠናቀቀ ስለሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሶፍት ዌር ምዝገባ ይደረጋል፡፡
- ✓ በቋሚ እና በአላቂ ንብረት ክፍል ስቶር ውስጥ ንብረቶችን የመጠበቅ፤ ሞዴል 19 እና 22 ገቢና ወጪ የሚሰራ በባለሙያ እጥረት ምክንያት የተፈጠረ ችግር በመሆኑ

በቀጣይ የሰዉ ሀይል በማሟላት የገቢና ወጪ የሚሰራ ባለሙያ ለያይተን የምንመድብ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

- ✓ ወጪ ተደርጎ ስራ ላይ ስላልዋለው ጀኔሬተር በተመለከተ በወቅቱ መብራት ሲጠፋ ለቢሮ አገልግሎት እንዲውል ተገዝቶ የነበረ ቢሆንም ካለው የጄኔሬተሩ የሀይል ማመንጨት አቅም አነሰተኛ ሆኖ ስለተገኘ በሌላ ትልልቅ ጄኔሬተር ተተክቶ መጠቀም መጀመራችን ወጪ ያልተደረገ ነው፡፡
- ✓ የሚወገዱ 49 ላብቶፕ አቀማመጥ በተመለከተ፡- የተመላሽ እቃ ጊዚያዊ እስቶር እንደመሆኑ መጠን በፍሳሽና በአቧራ ይበልጥ እንዳይጎዱ በማሰብና በጥንቃቄ ለመያዝ ሲባል ነው፡፡ ሆኖም በቀጣይ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ማስተካከያ እናደርጋለን፡፡
- ✓ በአላቂ ንብረት መጋዘን ውስጥ የሚገኘው የማሽን ድስት በተመለከተ፡- አዲስ እየተገነባ ላለው የተማሪዎች ምግብ ቤት እንዲገጠም የተገዛ ሲሆን በአላቂ ንብረት መጋዘን ውሰጥ በስህተት የተራገፈ በመሆኑና የምግብ ቤቱ ግንባታ እስኪጠናቀቅ ድረስ ነዉ ፡፡
- ✓ የመኪና ጎማና የመኪና ባትሪ የማስወገድ ስልጣን ያለው የኢፌዲሪ መን/ግ/ን/ማስ/አገ በመሆኑ መወገድ ያለባቸው ንብረቶች ዝርዝር መረጃ አስተላልፈን እስኪነሳልን በመጠበቅ ላይ የምንገኝ ሲሆን እንዲወገድልን የጠየቅንበት መረጃ በምርመራ ወቅት እርበን ያሳየን መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- ✓ በተመላሽ የቋሚ ንብረት ክፍል በር ፊት ለፊት የተከማቹ ንብረቶች በተመለከተ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች በተበታተነ ሁኔታ ይገኙ የነበሩ የሚወገዱ ንብረቶች እያሰባሰብንና እየለየን በነበርንበት ወቅት ያያችሁት ስለነበር በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚወገዱ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- ✓ በተመላሽ ቋሚ ንብረቶች መጋዘን ውስጥ ተጠግነው አገልግሎት የሚሰጡና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች አንድ ላይ የመቀመጣቸው ምክንያት በነበረብን የመጋዘን ጥበት እና አብዛኛዎቹ ንብረቶች ተጠግነው ከሚሰጡት ጥቅም በላይ በጥገና ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጡ በመሆናቸው ከሚወገዱ ንብረቶች ጋር የተቀመጡ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ✓ የተጠቃሚዎች ካርድ/user card/ በተጠቃሚዎች ያልተሰጠበት ምክንያት ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ ስለሆነ በቀጣይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር ከአይሲቲ ዳይሬክቶሬት ጋር በመሆን ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

- ✓ ለማስወገድ የተለዩ ንብረቶች በማኔጅመንት ውሳኔ መሰረት በማስወገድ ላይ ስንሆን ምርመራ በምታደርጉበት ወቅት ንብረቶቹ የተለየበት ዝርዝር መረጋ አቅርበን አሳይተናል
- ✓ የተማሪዎች ንብረት መጋዘን ውስጥ ለቢን ካርድ ማንጠልጠያነት ምቹ የሆነ መደርደሪያ ስለሌለ በቀጣይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር ክትትል እናደርጋል፡፡
- ✓ በሰው ሀይል እጥረት ምክንያት የተፈጠረ ችግር ስለሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለያይተን የምንወስድ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ✓ የተማሪዎች ክልኒክ በተመለከተ የቢን ካርድና ስቶክ ካርድ በተማሪዎች ክሊኒክ መድሃኒት መጠበቂያ ክፍል ውስጥ በአግባቡ ተደራጅቶ እየተሰራበት ነው ለአብነት ያህል በምርመራ ወቅት አቅርበን አሳይተናል
- ✓ መድሃኒቶችን የሚጠብቅ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 ገቢና ወጪ የሚሰራ ባለሙያ እጥረት ስለገጠመን በአንድ ባለሙያ እየተሰራ የነበረ ቢሆንም በቀጣይ ባለሙያ በመመደብ ለያይተን የምንሰራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ✓ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች ለማስወገድ ኮሚቴ የተዋቀረ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡
- ✓ የዩኒቨርሲቲው ትራክተር የእርሻ መኪና ታርጋ ቁጥርና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የማውጣት ሂደት ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በመሆን የሚሰራ በመሆኑ ስራው ተጀምሯል የማስተካከያ ስራ ይሰራል፡፡

8. ልዩ ልዩ፣

8.1.1 ግኝት፣ ትምህርት ላይ ያሉትን በተመለከተ፣

የትምህርት ዕድል ላገኙ የዩንቨርሲቲው መምህራን ለትምህርት የሚሄዱበት ሀገር/ተቋም፤መቼ ትምህርት ጀምረው መቼ እንደሚመለሱ የሚያሳይ ዉላቸዉ ላይ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ አገር በትምህርት ላይ ያሉ 163 መምህራን ለትምህርት የሄዱበት ጊዜ የማይታወቅ መሆኑን፣166 መምህራን ለትምህርት የሄዱበት ተቋም(የት እንደሚማሩ)የማይተወቅ መሆኑን፣174 መምህራን ትመህርታቸዉን ጨርሶ ወደ ስራ ገበታቸዉ የሚመለሱበት ጊዜ የማይታወቅ(ዉሉ ላይ አልተቀመጠም) መሆኑ በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

8.1.2 ስጋት፣

- ሰራተኞቹ የት እንዳሉና እስከ መቼ ትምህርታቸዉ ላይ እንደሚቆዩ እንዲሁም መቼ ወደስራ ገበታቸዉ እንደሚመለሱ ለማቅ ሊያስቸግር ይችላል።
- ተምሮ የጠፉት ሰራተኞች ልኖሩ ይችላሉ።

8.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞችን ለትምህርት ወደ ሌላ ቦታ ሲልክ ለትምህርት የሄዱበት ጊዜ፣ለትምህርት የሄዱበት ተቋም እና ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚመለሱበትን ቀን በትክክል ማስቀመጥ ይኖርበታል።
- ለትምህርት የሄዱበት ጊዜ፣ለትምህርት የሄዱበት ተቋም እና ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚመለሱበትን ቀን በትክክል ታውቆ ውሉ ተስተካክሎ ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል።

8.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የትምህርት እድል ተሰጥቷቸው በመማር ላይ የሚገኙ መምህራኖች በፈረሙበት የውል ቅጽ የተሟላ መረጃ ያልያዘ መሆኑ እንደ ጉድለት ወስደነው በቀጣይ በተሰጠው አስተያየት መሰረት የውል ቅጽን አስተካክለን የምንሰራው መሆኑን እናሳውቃለን።

8.2.1 ግኝት፣ የውስጥ ኦዲት አሰራርን እና አደረጃጀት በተመለከተ፣

የፌዴራል መንግስት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 ክፍል አምስት የውስጥ ኦዲት ዕቅድና ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ ላይ በንዑስ አንቀፅ 3 በኦዲት ዕቅድ መሰረት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 30፣የሁለተኛው ሩብ ዓመት እስከ ጥር 30 የሶስተኛው ሩብ አመት እስከ ሚያዚያ 30፣የአራተኛ ሩብ ዓመት እስከ ነሀሴ15 ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ እንደሚገባ ይገልፃል፣በተጨማሪም የ2009 ፐርፎረማነስ/ክዋኔ/ ኦዲት ስለመደረጉ፣ለፖርፎርማንስ/ክዋኔ/ እና ለፋይናንሻል ኦዲት የተሟላ የስራ ወረቀት /working paper/ ስለመኖሩ እንዲሁም በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ኃይል ስለመኖሩ ኦዲት ሲደረግ፣

- የ2009 በጀት አመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 30 ወጪ ሆኖ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ሲገባ ጥር 29/2009 መላኩ፣የሁለተኛው ሩብ ዓመት እስከ ጥር 30 ወጪ ሆኖ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ሲገባ መጋቢት 29/2009 መላኩ፣የሶስተኛው ሩብ አመት እስከ ሚያዚያ 30 ወጪ ሆኖ

ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ሲገባ ግንቦት 14/2009 መላኩ፣የአራተኛ ሩብ ዓመት እስከ ነሀሴ 15 መላክ ሲገባ ህዳር 14/03/2010 የተላከ መሆኑን፡፡

- የመስራ ቤቱ አሰራር ከብቃት፣ከውጤታማ እንዲሁም ከኢኮኖሚ አንፃር ኦዲት ያልተደረገ መሆኑን፣
- የተሟላ የስራ ወረቀት/working paper/ ማለትም ስለተከናወነው ስራ በወጪ፣በገቢ፣በተሰብሳቢ፣ተከፋይ ሂሳቦች ወዘተ የሚያሳይ መርሀ ግብር /audit programe/፣ የሳምፕል መጠን እና የሳምፕል አመራረጥ የሚያሳይ የስራ ወረቀቶች የሌሉ መሆኑ፣
- የውስጥ ኦዲት ክፍል በበቂ የሰው ኃይል ያልተደራጀ መሆኑ፡፡
- ጥር 29/2009 በዉስጥ ኦዲት ተዘጋጅቶ ለቀረበዉ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት ገጽ 5 ላይ የዉስጥ ኦዲት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠዉ ስልጣንና ሀላፍነት መሰረት ይላል አዋጁ ለኦዲት ስራ ተጠይቆ ባለማቅረቡ ለግኝቶቹ የተቀመጠዉ ክራይቴሪያ (አዋጅ) ትክክል መሆኑን ለመገምገም ያልተቻለ መሆኑን፡፡

8.2.2 <u>ስጋት፣</u>

- የመስሪያ ቤቱ አሰራር ውጤታማ ፣በብቃት እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ አፈፃፀም ላይ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አያስችልም፣
- ግድፈቶች ቢከሰት በጊዜው የማስተካከያ እርምጃ እንዳይወስድ ላያደርግ ይችላል፣ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡
- ሰራተኞቹ የሚጠቀሙበት የመብራትና ውሃ አገልግሎት ክፍያ አላግባብ የመ/ቤቱን ወጪ ሊያንር ይችላል፡፡

8.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ዩኒቨርሲቲው ለወደፊቱ የውስጥ ኦዲት አገልግሎት በመመሪያው በተሰጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ፐርፎርማንስ/የክዋኔ/ ኦዲት ማከናወን ይጠበቅበታል፣
- ለኦዲቱ የተሟላ የስራ ወረቀቶች በማዘጋጀት እና በማደራጀት በፍይል መያዝ ይኖርበታል፣
- የዉስጥ ኦዲት ስራ ክፍል በበቂ የሰው ኃይል፣ተገቢዉ የሙያ ብቃት፣ዕዉቀትና ክህሎት ባላቸዉ ባለሙያዎች እንዲደራጅ የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠዉ ስልጣንና ሀላፍነት ተብሎ ሪፖርት የተደረገ ሪፖርቱ የመስተካከያ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

8.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- ✓ ሪፖርቱ የዘገየበት ምክንያት በተደጋጋሚ የአይቤክስ ሲስተም ብልሽት ያጋጥም ስለነበር የፋይናንሻል እንቅስቃሴ ሪፖርት በዛው ልክ ስለሚዘገይ እንዲሁም በቂ ክህሎት ያለው የባለሙያ እጥረት በመኖሩ ምክንያት የሪፖርት

መዘግየት ያጋጥም የነበረ ሲሆን በአሁን ወቅት የአይቤክስ ችግር ከሞላ ጎደል የተፈታ ሲሆን የባለሙያ እጥረት በሂደት በማሟላት ችግሩን ሙሉ ለሙሉ ለመቅረፍ ጥረት እናደርጋለን፡፡

- ✓ የክዋኔ ኦዲት አስመልክቶ የቀረበው ግኝት በተመለከተ በባለሙያ እጥረት ሳይሰራ የቆየ ቢሆንም በቀጣይ ካሉን ውስን ባለሙያዎች መካከል መርጠን ስልጠና እንዲያገኙ እና ከአቻ ዩኒቨርስቲዎች ልምድ በመቅሰም በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ተግባር የምንገባ መሆኑን እንገልፃለን
- ✓ የስራ ወረቀት /Working Paper/ እና የናሙና አመራረጥ አስመልክቶ የተሟላ ባይሆንም በጅምር ደረጀ ፋይል ተከፍቶ እያደራጀን የምንገኝ ሲሆን እንደ አጠቃላይ የተፈጠረው ክፍተት በባለሙያ ግንዛቤ እጥረት በመሆኑ በቀጣይ ስልጠና በማመቻቸት የማብቃት ስራ በመስራት በተሟላ ሁኔታ የምንሰራው መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ✓ የውስጥ ኦዲት በበቂ የሰው ሀይል/በባለሙያ ያልተደራጀው በተደጋጋሚ የቅጥር ማስታወቂያ ቢወጣም በገበያ ላይ ማግኘት ባለመቻሉ ምክንያት የተፈጠረ ክፍተት በመሆኑ እየገለፅን በተለያዩ ጊዝያት ያጣናቸዉ ማስታወቂያዎች የሰዉ ሀብት ቢሮ ዉስጥ ማህደር ዉስጥ ተያይዘዉ ይገኛሉ፡፡
- ✓ ጥር 29/2009 በውስጥ ኦዲት ተዘጋጅቶ በተላለፈው ሪፖርት ላይ በገጽ 5 ስለተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 669/2002 የተባለው በታይፐ ስህተት የተፈጠረ መሆኑን እየገለፅን ለመጥቀስ ፈልገነዉ የነበረዉ አንቀጽ 649 ለማለት ተፈልጎ የነበረ መሆኑን እንገልፃለን፡

8.3.1 ግኝት፣ ውል የሚጠናቀቅበት ቀን ያልተጠቀሰ ስለመሆኑ፣

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የመንግሥት መ/ቤት ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ውሎችና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉ መጠናቀቁን ማረጋገጥ አለባቸው በማለት ይገልፃል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ዩኒቨርሲቲው በብር 850,000.00 የተማሪዎች ምግብ ቤት በዘመናዊ መልኩ እንዲደራጅለት ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር ውል ገብቶ ክፍያ የተፈጸመለት ሲሆን ዩኒቨርሲቲዉ ውሉ የሚጠናቀቅበት ቀነገደብ ያላስቀመጠ መሆኑን፡፡ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

- ✓ የውል ስምምነት ሲገቡ ውል የገቡበትን ቀን 05/12/2007 ዓ.ም ብለው ቢቀመጥም ውሉ የሚጠናቀቅበት ቀነገደብ ባለመቀመጡ ውል ተቀባይ በውሉ ቀነገደብ ውስጥ ግዴታውን መወጣቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

8.3.2 ስጋት፣

ውል ተቀባይ ውሉን በአግባቡ ባለመፈፀሙ ምክንያት በውል ሰጪ ላይ ለሚመጡ ለማናቸውም ኪሳራዎች በሕግ ፊት ተጠያቂ ስለመሆኑና ሥራዎቹ በትክክል ስለ መሰራታቸው ማረጋገጥ የማይቻል ከመሆኑም ባሻገር የመንግሥት ገንዘብ እንዲመዘበር በቀላሉ በር ሊከፍት ይችላል፡፡

8.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ውሉ የተሟላ መሆኑን በማየትና የተፈለገው ሥራ በትክክል ስለመሰራቱ ከባለሙያዎች የፅሑፍ ማረጋገጫ መኖሩን በማረጋገጥ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

8.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ዘመናዊ የተማሪዎች ምግብ ቤት ስናደራጅ የማማከር አገልግሎት እንዲሰጡን ውል የገባን ቢሆንም ውሉ የሚጠናቀቅበት ጊዜ ያልተቀመጠው የማማከር ስራው እቃው በሚቀርብበት ጊዜ እና የኢንስታሌሽን ስራ በሚሰራበት ጊዜ ይወስናል በሚል ታሳቢ ተደርጎ በመሆኑ ይህንን እንደ ክፍተት በመውሰድ ከማንኛውም ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ውል ስንፈጽም ውሉ የሚጠናቀቅበት ጊዜ እያስቀመጥን እየሰራን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

8.4.1 ግኝት፣ ድርጅቶቹ ከአቅም በላይ ችግር ሲያጋጥማቸዉ በውሉ መሰረት በ3 ቀን ውስጥ በፅሑፍ ያላሳወቁ ስለመሆኑ፣

የፌደራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 29.2 የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው የመንግሥት መ/ቤቱ አካል አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል በሚል ይገልፃል፡፡

እንዲሁም ዩኒቨርሲቲዉ እና ድርጅቱ የተዋዋሉት ውል አንቀጽ 6 ላይ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ውል ተቀባይ(የውል ሰጪ)በ3 ቀን ውስጥ ለውል ሰጪ(ለውል ተቀባይ)በፅሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ሆኖም ግን በተቻለ መጠን ውሉን ለመፈፀም የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት በማለት ይገልፃል፡፡ በዚህ መመሪያ እና ውል መሰረት ድርጅቶቹ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች በ3 ቀን ውስጥ ለዩኒቨርሲቲዉው በፅሑፍ ማሰወቃቸውን ለማወቅ ኦዲት ሲደረግ፣

- በቀን 21/2/2009 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 568370 በሂሳብ መደብ 6313 ብር 1,249,332.16 የዳቦ ሊጥ መቁረጫ ማሽኖች ግዥ ከበረከት ክፍሌ አስመጪና ላኪ ኃ/የተ/የግ/ማ የተከፈለዉ በዉሉ መሰረት እስከ 13/09/2008 ንብረቶቹን ገቢ ማድረግ እንዳለበት ውል ተዋውሏል፣ድርጅቱ የውሉ ቀነገደብ ከለቀ በኃላ 276 ቀናት በማሳለፍ በቀን 15/06/2009 ከአቅም በላይ ችግር እንዳጋጠመ በመመልከቱ ዩኒቨርሲቲው በቀን 20/06/2009 እስከ የካቲት 20/2009 እንድራዘምለት የፈቀደለት መሆኑን፣

- በቀን 20/6/2009 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0846325 በሂሳብ መደብ 6314 ብር 1,519,999.95 የላብራቶሪ ዕቃዎች ግዥ ከኢልሀም ካሳ አስመጪ ኃ/የተ/የግ/ማ የተከፈለዉ በዉሉ መሰረት እስከ 02/06/2008 ንብረቶቹን ገቢ ማድረግ እንዳለበት ዉል ተዋዉሏል፣ድርጅቱ የዉሉ ቀነገደብ ከለቀ በኃላ 71 ቀናት በማሳለፍ በቀን 14/08/2008 ከአቅም በላይ ችግር እንዳጋጠመ በመመልከቱ ዩኒቨርሲቲው በቀን 14/02/2009 እስከ መስከረም 30/2009 እንድራዘምለት የፈቀደለት መሆኑን፣

በአጠቃላይ ድርጅቶቹ ከአቅም በላይ ችግር ሲያጋጥማቸው በውሉ መሰረት በ3 ቀን ውስጥ በፅሑፍ የማያሳዉቃቸውና የውሉ ቀነገደብ ከላፈ በኃላ እስከ 276 ቀይቶ ያመለከቱት ድርጅቶች መኖራቸውን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡

8.4.2 <u>ስጋት፣</u>

ዩኒቨርሲው በውሉ መሰረት ግዴታውን መወጣት ካልቻለ አገልግሎቱ ጊዜውን ጠብቆ እንዳይሰጥ ከማድረጉም ለብልሹ አሰራር በቀላሉ በር ሊከፍት ይችላል፡፡

8.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በውል ስምምነት ወቅት ውል ሰጪው ለውል ተቀባይ ዕቃዎችን በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያስገባ በተሰጠው ቀን ገደብ ጊዜ ውስጥ ማስገባቱን በመከታተል አቅራቢ ድርጅቶች የውል ማስረዘሚያ ጊዜ ሲጠይቁ በውሉ ጊዜ ገደብ ውስጥ መጠየቃቸውን የማረጋገጥ ሥራ እንዲሠራ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

8.4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ድርጅቶች ከአቅም በላይ ችግር ሲያጋጥማቸው አብዛኛውን ጊዜ ውል ከማለፉ በፊት በደብዳቤ ይጠይቁና የ3ኛ ወገን ማስረጃ አያይዛችሁ አቅርቡ ተብለው በሚቀጥለው ጊዜ ሲመጡ የውሉ ጊዜ ያለፈ ቢሆንም መጀመሪያ ያመለከቱበትን ደብዳቤ ትተው በአዲስ ጽፈው ስለሚያመጡና በዛው አግባብ ስለተስተናገዱ የተፈጠረ ክፍተት ከመሆኑም በተጨማሪ በአብዛኛው እንደ አገር የሚታወቀው በምንዛሬ እጥረት ምክንያት የተከሰበት ቢሆንም ክፍተቱን እንደ ክፍተት አይተነዉ አሁን ግን አርመን እየሠራን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

8.5.1 <u>**ግኝት፣**</u> <u>**የተከፈለው ውሎ አበል እና ደመወዝ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ያልተቻለ፣**</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 10 ንዕስ አንቀጽ 8 የመንግስት ሠራተኞች ደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ ወይም ወጪ ከመደረጉ በፊት ሰራተኞቹ በስራ ላይ ለመሆናቸዉ የቀረበ ማረጋገጫ መኖር እንዳለበት ይገለፃል ሆኖም ዩኒቨርሲቲዉ የሰራተኞች የስራ ሰዓት መቆጣጠሪያ በ2009 በጀት ዓመት የፋይናስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሰራተኞች እና ለሰዉ ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሰራተኞች ለኦዲት ስራ ተጠይቆ ባለማቅረቡ በ2009 በጀት ዓመት ለሰራተኞቹ የተከፈለዉ ውሎ አበል እና ደመወዝ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፡፡

8.5.2 ስጋት፣

- የመ/ቤቱ ሰራተኞች የመንግስትን ስራ ሰዓት ለመንግስት ስራ ብቻ ላያዉሉ ይችላሉ፡፡
- በ2009 በጀት ዓመት ለሰራተኞች የተከፈለ ዉሎ አበል እና ደመወዝ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ሊያስቸግር ይችላል፡፡

8.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የዩኒቨርሲቲዉ ስራ አመራር በ2009 በጀት ዓመት የሁለቱ ዳይሬክቶሬት ሰራተኞች የስራ ሰዓት መቆጣጠሪያ የማይፈርሙበት ሚክንያት አጣርቶ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ለሁለቱም ዳይሬክቶሬቶች የስራ ሰዓት መቆጣጠሪያ እንዲኖራቸዉ ጥብቅ ቁጥጥር ሊያድርግ ይገባል፡፡

8.5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ ሰአት መቆጣጠሪያ በተመለከተ ምንም እንኳን ሰራተኛው ዘወትር በስራ ገበታው ተገኝቶ ዕለታዊ ተግባሩን እያከናወነ መሆኑን ብናረጋግጥም የሠዓት ፊርማ ሳይቆራረጥ መፈረም የነበረበት መሆኑን ተገንዝበን ከታህሳስ ወር 2010 ጀምሮ ወጥነት ባለው ሁኔታ እተፈረመ መሆኑንና መረጃውንም በተደራጀ መልኩ እየያዘን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

8.6.1 እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች፣

- በ2008 ዓ.ቆጠራ ሲካሄድ ጠፍተዋል ተብለው የተገለፁ ንብረቶች ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተር ብዛት 29፣ ላፕ ቶፕ ብዛት 6፣የምግብ ቤት ጠረጴዛ ብዛት 13፣ ሚድየም ሀይ ባክ ወንበር ብዛት 12፣ ቴሌዝዥን ብዛት 3
- 7 ኮምፒውተሮች፣ የሰባቱ RAM፣የኮምፒውተር ስፒከሮች (ብዛት 6)፣mouse(ብዛት 6)፣እንዲሁም አንድ LCD Projector፣ሪሲቨር ከፋሲሊቲ ልማት አስ/ዳ/ዳይሬክተር በቁጥር ወ/ዩ/5235/41/07 በቀን 20/08/07 ለወልቅጤ ከተማ ፖሊስ የተገለፀ ቢሆንም አሁን ድረስ መፍትሄ ያላገኘ መሆኑ፡
- አጋፔ ካፍቴሪያ የቤት ኪራይ ከሚያዚያ 2007 እስከ ሰኔ 2007 ብር 46,732.62፣እንዲሁም ከጥቅምት 2008 እስከ ግንቦት 2008 ብር 124,620.32 በድምሩ 171,352.94 ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ፡፡

- ሽናት ሽቀጣ ሽቀጥ የተባለውም በ2007 እና 2008 ዓ.ም በድምሩ ብር 7,351.95 ለዩኒቨርሲቲው የቤት ኪራይ ገቢ ያላደረገ መሆኑ፡-
- በ2008 በጀት ዓመት ውስጥ ከካፍቴሪያ፣ከሽቀጣ ሽቀጥ፣ከውበት ሳሎን፣ከፅህፈትና ፎቶ ኮፒ አገልግሎት መሰብሰብ የነበረበት ብር 11,177.9 ተሰብስቦ ገቢ ያልተደረገ መሆኑን፡፡
- ብር 75,240.00 በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ በሚከበረው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት እና የ2007 ዓ.ም. የተማሪዎች ምረቃ በዓል በድምቀት ለማክበር በማለት የበዓሉ ቆይታ ጊዜው ሳይገለጽና የተሳታፊዎች ስማቸው ተመሳሳይ በሆነበት ሁኔታ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን፡፡
- ብር 104,376.00 ዩኒቨርሲቲው በመደበኛ የጥበቃ ሥራ ላይ ተሠማርተው ለሚሰሩ ሰራተኞች ሥራው በትክክል በትርፍ ሰዓታቸው ለመስራታቸው የሚያሳይ የሰዓት መቆጣጠሪያ ፊርማ እና በቀን የሚከፈላቸው የገንዘብ መጠን በሌለበት እንዲሁም ለማን እና እንዴት እንደሚከፈል የሚያሳይ የተሟላ የሰነድ ማስረጃ ሳይኖር ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ዩኒቨርሲቲው ለመምህራን የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት ሰጥቷቸው እያለ በተጨማሪ ለ75 (ሰባ አምስት) መምህራን በየወሩ ሀምሌ 2007- ሰኔ 2008ዓ/ም ጠቅላላ ብር 615,600.00 የቤት አበል ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች በሪፖርቱ ላይ በተገለፀው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያለ አግባብ ክፍያ የተፈፀመባቸው ተመላሽ መሆን እንዳለባቸው የተገለፀ ቢሆንም እስከ አሁን ገንዘቦቹ ተመላሽ አለመደረጋቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

8.6.2 ስጋት፣

በኦዲት ግኝቶች ላይ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜን ለኪሳራ ሊዳርግ የሚችል ነው፡፡

8.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜ የወጣባቸው በመሆኑ በኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ የሥራ አመራሩ፣ የዩኒቨርስቲው ቦርድና የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

8.6.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- ✓ በ2008 ቆጠራ ወቅት ጠፍተዋል ተብሎ የተገለፀው ቆጠራ በሚካሄድበት ወቅት አጠቃላይ ገቢ እና ወጪ ተመዛዝኖ የታየ ልዩነት ሲሆን ይህም የተከሰተው

የተጠቀሱት ንብረቶች ወጪ አድርገው ሳያስቆጥሩ እና ሳያስረክቡ ያለምንም ክሊራንስ ስራቸውን ለቀው በሄዱ ሰራተኞች ምክንያት የተፈጠረ ችግር ሲሆን በቀጣይ ግለሰቦቹን ለይተን በህግ አግባብ ሄደን የምናስመልስ መሆኑን እንገልጻለን፡፡ የጠፋ ንብረቶች አስመልክቶ ለፖሊስ ክስ ተመስርቶ አሻራ መወሰድ ባለበት ቦታ ጭምር አሻራ ተወስዶ ምርመራ ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም እስካሁንም ፖሊስ የደረሰበትን ተጨባጭ ማስረጃ ያልገለፀልን በመሆኑ ምላሹን እየተጠባበቅን የምንገኝ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

- ✓ የአጋፔ ካፍቴሪያ ያልከፈለው የቤት ኪራይ በጥቅሉ ብር 171,352.94 በተመለከተ በዩኒቨርስቲው ህግ አገልግሎት በኩል ክስ እንዲመሰረት ደብዳቤ የተፃፈ ሲሆን በቀጣይ በህግ የሚወሰን ይሆናል፡፡
- ✓ ሸናት ሽቀጣ ሸቀጥ ያልከፈለው የቤት ኪራይ ብር 7,351.95 በተመለከተ ይህም በማጣራት ሂደት ላይ የምንገኝ ሲሆን ከማጣራቱ ሥራ በኂላ በህግ አግባብ የሚኬድበት መሆኑን እንገጻለን፡፡
- ✓ በ2008 በጀት ዓመት ውስጥ ከካፍቴሪያ፣ ከሸቀጣሸቀጥ፣ ከውበት ሳሎን፣ ከጽህፈትና ፎቶ ኮፒ የቤት ኪራይ ያልተሳሰበ ብር 11,177.90 በተመለከተ ተከራዮቹ በአቅራቢያቸዉ ባንክ ገቢ ያደረጉ ቢሆንም ደረሰኙ ፋይናስ ክፍል አቅርበዉ ደረሰኝ ሳያስቆርጡ በመቅረታቸዉ የተፈጠረ ክፍተት ስለሆነ በአጭር ጊዜ ዉስጥ የባንክ ደረሰኛቸዉ አቅርበዉ የገቢ ደረሰኝ እንዲያስቆርጡ የምናደርግ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- ✓ ከአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ቀን አከባበር እና የ2007 የተማሪዎች የምርቃ በዓል ጋር ተያይዞ ፕሮግራሞቹ የተካሄዱት በተለያየ ጊዜ እና ፕሮግራም ሲሆን ለበዓሉ ድምቀት እንዲሰጡ ታስቦ የጉራጌ ዞን ባህል ኪነት ቡድን በሁለቱ ከላይ በተጠቀሱት ፕሮግራሞች ልምምድ እና ዝግጅት ያደረጉ በመሆኑ እንዲሁም ከ7-10 ባሉት ቀናት ውስጥ በተለያዩ የችግኝ ተከላ በተካሄደባቸዉ ወረዳዎች በመገኘት ቅስቀሳና ድምቀት በመስጠት የቆዩ በመሆናቸው የተከፈላቸዉ ክፍያ መሆኑ ታውቆ ከግኝት እንዲወጣልን እየጠየቅን በቀጣይ ተመሳሳይ ክፍያ ስንፈፅም ዝርዝርና ገላጭ መረጃዎችን የምናያይዝ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

- ✓ ለጥበቃ ሠራተኞች ስለተከፈለው ተጨማሪ ስራ ክፍያ በተመለከ የጥበቃ ሰራተኞች ቋሚ ሰራተኞች ሳይሆኑ በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ማህበር ዋልያ የጥበቃ ማህበር ሲሆን የጥበቃውን ስራ በማህበሩ ህገ-ደንብ መሰረት በየ24 ሠዓት እየተቀያየሩ በሺፍት እየሠሩ ባሉበት ወቅት በወቅቱ በአገሪቱ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ተፈጠረ በነበረው የፀጥታ ችግር ወደ ዩኒቨርስቲያችን ተሸጋግሮ የመማር ማስተማር ስራ እንዳይስተጓጎልና ንብረት እንዳይወድም ለማድረግ ከውጪ ሌላ ሀይል ለማምጣት ታስቦ ጉዳዩ በጥልቀት ሲታሰብ የሚጠይቀን ወጪ ከፍተኛ እንደሚሆን ስለታመነበት እንዲሁም በተማሪዎች ዘንድ ልዩ ፍርሃትና ስጋት ተፈጥሮ ትምህርታቸውን አቋርጠው ሊወጡ ይችላሉ በሚል ስጋት ቀድሞ ግቢዉን ይጠብቁ የነበሩ ከዩኒቨርስቲው ከ20 እስከ 30 ኪ/ሜ ራድየስ ርቀው የሚገኙ የዋልያ ጥበቃ ማህበር አባላት ከመደበኛ ስራ ስርዓታቸው ውጪ በእረፍት ሰዓታቸው የጥበቃውን ስራ ከመደበኛ የጥበቃ ተረኞች በተደራቢነት እንዲሰሩ አድርገን የቦታው ዝቅተኛ አበል በቀን 98 ብር ሂሳብ በቆዩበት ቀን ተባዝቶ የተከፈላቸው ሲሆን ይህን በማድረጋችን ምንም አይነት የፀጥታም ሆነ የንብረት ውድመት ሳይከሰት ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ የትምህርት ዘመኑ በተሳካ ሁኔታ አጠናቀናል፡፡ በወቅቱ ከነበረው ስጋትና አለመረጋጋት አንፃር ከክፍያ ሰነዱ ጋር መያያዝ የነበረበት አቴንዳንስና ሌሎችም ተያያዥ አባሪ መረጃዎች አለማያያዝ እንደ ክፍተት ተወስዶ ከግኝቱ በኃላ ከስህተቱ ተምረን ጥንቃቄ በማድረግ ላይ የምንገኝ ስለሆነ ግኝቱ እንዲሰረዝልን እንጠይቃለን፡፡

- ✓ ለመምህራኖች ስለተከፈለው የቤት አበል ክፍያ ብር 615,600 በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ በግኝቱ ላይ ዩኒቨርስቲው ለመምህራን የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት ሰጥቷቸዉ ነበተጨማሪ የቤት አበል እንደ ተከፈላቸዉ የተገለጸዉ ዩኒቨርስቱው በምንም መልኩ ከመምህራኖቹ ጋር ተዋውሎ ቤት ያልሰጣቸው መሆኑ፣ በወቅቱ ዩኒቨርስቲው ለገዛቸዉ ኮንደምኒየም ቤቶች በ2007 ዓ.ም ሙሉ ክፍያ የፈፀመ ቢሆንም ብዙ የግንባታ ቀሪ ስራዎች የነበሩበት መሆኑ፣ ምንም አይነት የመሰረተ-ልማት ማለትም የመብራት፣ የውሃ፣ የመንገድ ዝርጋታ ያልነበረው በመሆኑ፣ በአጠቃላይ የተገዙት ቤቶች በውስጥ መሟላት ከነበረባቸው የመፀዳጃ ቤት፣ የመስኮት እና በር ያልተገጠመ ኮርኒስ ያልነበረው የሊሾ ስራ ያልተጠናቀቀ የነበረ በመሆኑ በወቅቱ ቤቶቹ በነበሩበት ሁኔታ የሰው ልጅ ያኖራል ብለን ለመስጠት ተቸግረን ባልንበት ወቅት መምህራኖቹ

በከተማው ዉስጥ በተፈጠረዉ የኪራይ ቤት እጥረት ችግር አንፃር በተፈጠረባቸው ስሜት ከዩኒቨርስቲው ጋር ምንም አይነት ውይይትም ሆነ ውል ሳይፈፅሙ በገዛ ፍቃዳቸው እና በራሳቸው ወጪ ያልተሟላውን የግንባታ ስራ አነስተኛ ጥገና በማድረግ እየኖሩ ስለነበረ የቤት አበል ክፍያቸውን ለማቋረጥ የሚያስችለን የህግ አግባብ አልነበረንም፡፡ ሆኖም በቤት እጥረት ምክንያት የመምህራን ፍልሰት ለመግታት በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን አስወጥተንና አድስን የመኖርያ ቤት አስተዳደር መመሪያና ደንብ አዘጋጅተን መምህራኖች በግልፅ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ተወዳድረው ካሸነፉት ጋር ውል ተዋውለን ከአሸናፊ መምህራኖች ጋር ውሉ ከተፈፀመበት ወር ጀምሮ የቤት አባላቸው ያቋረጥን ስለሆነ ቀድሞ በራሳቸው ወጪ አውጥተው ቤቱን በመጠገን ዩኒቨርስቲው ባልሰጣቸው ቤት ቤት ሰጥተናችሁ ነበር በሚል የቤት አባላቸውን ለማስመለስ የተቸገርን መሆኑን፣

በመጨረሻም ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!